# አዲስ ዘመን

እንድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 006 መስከረም 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

በቡና ልማትና ንግድ ዘርፍ ውጤታማ ለነበሩ ባለድርሻ አካላት እውቅና ተሰጥቷል

# የቡና ሀብታችን ብዙ ያልተጠቀምንበት በመሆኑ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብትሆንም ብዙ ያልተጠቀምንበት ሀብት በመሆኑ በትኩረት ሊሰራበት እንደሚገባ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ፡፡ ለቡና ውጤታማነት ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው 267 ባለድርሻ አካላት ከፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እጅ እውቅና እና ሽልማት ተቀብለዋል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ «ቡናችን ለአብሮነታችንና ለብልጽግናችን» በሚል መሪ ቃል የቡና ቀን ትናንት ሲከበር ባደረጉት ንግግር፤ በመደጋገፍና በመተባበር በልማት ላይ ከሰራን የማይደረስበት የዕድገት ምዕራፍ የለም፡፡ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብትሆንም ብዙ ያልተጠቀምንበት ሀብታችን ነው፡፡ በቡና የውጭ ምንዛሬ እንዲገኝ ላደረጉ አካላት እውቅና መስጠት ስራቸውን በማሳወቅ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

«የቡና ሀብታችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “አሸባሪው ትህነግ ለሰላም ቁርጠኛ ቢሆን ሦስተኛውን ዙር ጦርነት አይጀምርም ነበር”

- አቶ ሱራፌል ጌታሁን
የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትህነግ ለሰላም ቁርጠኛ ቢሆን ሶስተኛውን ዙር ጦርነት አይጀምርም ነበር ሲሉ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን አስታወቁ።

አቶ ሱራፌል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሽብር ቡድኑ ለሰላም ቁርጠኛ ቢሆን በመንግስት በኩል ተደጋጋሚ የሰላም እድሎች ተሰጥተውት እያለ ጦርነት አይከፍትም ነበር፤ ንጹሃንንም አይጨፈጭፍም ነበር።

አገር የማፍረስ፣ መሰረተ ልማቶችን ማውደም፣ ከኢትዮጵያ ጠላት አገሮች ጋር አብሮ መውጋት የሽብር ቡድኑ መገለጫ ባህሪያት ናቸው ያሉት አቶ ሱራፌል፤ የሚመራው በሚጋልቡት ፈረሶች ስለሆነ ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን ቁርጠኛ አይሆንም ብለዋል።

«አሸባሪው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “አሸባሪው ትህነግ በድብቅ በርካታ የጦር መሳሪያዎችን በማስገባት ሦስተኛ ዙር ወረራ ቢፈጽምም ምኞቱ መክኗል”

- አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትህነግ በርካታ የጦር መሳሪያዎችን በድብቅ ከውጭ ቢያስገባም፤ ድል በጦር መሳሪያ ብቻ ስለማይገኝ እሱ እንዳሰበው ኢትዮጵያን ማፍረስ እንዳልቻለ እና በሁሉም አቅጣጫ ባስተናገደው ከባድ ምት የተመካበት ጦር መሳሪያ ከንቱ ሆኖ ምኞቱ መምከኑን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ተናገሩ፡፡

አቶ አንዳርጋቸው በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ ቡድኑ በተደጋጋሚ ሲያደርጋቸው የነበሩ ወረራዎች ሲከሽፉበት ቆይተዋል፡፡ ለአብነትም ከዚህ በፊት ወደ አማራ ክልል እና ወደአፋር ክልሎች ሁለት ጊዜ ወረራ ፈጽሟል፡፡ ሆኖም በእነዚህ ወረራዎች ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶበታል፡፡

«አሸባሪው ትህነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የማህበራዊ ሚዲያዎችን ስንጠቀም ገንቢ ሚና ያላቸውን ለይተን መሆን አለበት

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- “የማህበራዊ ሚዲያዎችን መረጃ ከመጠቀማችን በፊት ገንቢነት ያለው መረጃ የሚያሰራጩትን መለየት እንደሚገባ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሒም ቱፋ ተናገሩ፡፡

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት አንደኛ መደበኛ ጉባኤውን ሲያሂድ የተገኙት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም እንደገለጹት፤ በየትኛውም አካል በሚዘወሩ ማህበራዊ ሚዲያዎች የምናገኘውን መረጃ ከመጠቀማችን በፊት እውነተኛና ተዓማኒነቱን መለየት ያስፈልጋል፡፡

ሚዲያዎቹ በመረባቸው የሚበትኑት መረጃ ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ ያለው ሀቅን መለየትና ማስተንተን

«የማህበራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሼህ ሐጂ ኢብራሒም ቱፋ፤






ከሰብአዊ እርዳታው በስተጀርባ ያለው ሴራ

ገጽ 6

# አሸባሪው ትህነግ በትግራይ ህዝብ ላይ የፈጸመው ጭካኔ መሳውን ኢትዮጵያዊ ያሳመመ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ሰብአዊ ድጋፍን ለጦርነት በማዋል በትግራይ ህዝብ ላይ የፈጸመው ጭካኔና ሰቆቃ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ እያሳመመ ይገኛል ሲሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ ገለፁ።

ኡስታዝ ካሚል ለአልጀዚራ ቴሌቪዥን እንዳብራሩት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር እንዲቀረፍ ካስፈለገ ጦርነት የከፈተው የትህነግ ቡድን ለሰላማዊ መፍትሄው ራሱን ሊያዘጋጅ ይገባል።

ከአንድ አመት በፊት በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ የነበረው ጦርነት፣ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲፋጠን በሚል በኢትዮጵያ መንግስት ተናጠላዊ የተኩስ ማቆም ውሳኔ ቢደረግም በአሸባሪው ትህነግ ጦረኝነት ምክንያት የተኩስ አቁሙ ዘላቂ ሊሆን አለመቻሉን ገልጸዋል።

ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን መንግስት ተናጠላዊ ተኩስ ማቆም ማካሄዱን፣ ለሰብአዊ ድጋፍ ስርጭቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ላይ ሲሰራ መቆየቱንም አስታውሰዋል።

መንግስት የሰላም አማራጭን በመዘርጋት ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ያሉበት ቡድን በማዋቀር በየትኛውም ቦታና ሁኔታ የሰላም አማራጭ ሊደረግ እንደሚችል መወሰኑን አንስተዋል።

ኡስታዝ ካሚል የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላማዊ አማራጩ ያለውን ዝግጁነት ቀደም ብሎ ለህዝብና ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳወቁን አብራርተው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አንድ ብሄራዊ መንግስት አንድ የመከላከያ ሃይል እንዲሁም የክልል አስተዳደሮች የመሆናቸው ጉዳይ ህገመንግስታዊ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ አይገባም ብለዋል።

በአሸባሪው ሕወሓት በኩል የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት የሚፈታተኑ በርካታ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር ንግግር ያለማድረግ ጥረት መኖሩን ያብራሩት ኡስታዝ ካሚል፤ የኢትዮጵያ መንግስት አሁንም የሰላም አማራጩን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ማስረዳታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።



ኡስታዝ ካሚል ሸምሱ



አቶ የሱፍ ኢብራሂም፤

## ግዢዎችን በማሸጋሸግ ወደ 19 ሚሊዮን ብር ማዳን ተችሏል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሊፈጸሙ የነበሩ ግዢዎችን እንዳይፈጸሙ በማገድ እና ያለአገልግሎት የተቀመጡትን በማሸጋሸግ ወደ 19 ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ማዳን መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን የ2014 በጀት አመት የዕቅድ አፈፃጸም ግምገማና የዕውቅናና ሽልማት መርሀ- ግብር አካሂዷል።

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ የሱፍ ኢብራሂም እንደተናገሩት፤ በተደጋጋሚ ግዢዎች ምክንያት የሃብት ብክነት እንዳይፈጠር የተለያዩ ሥራዎችን ስንሠራ ቆይተናል። በዚህም ተቋማችን እንደሙከራ ጣልቃ በገባባቸው የመንግስት ግዢዎች በኩል ወደ 19 ሚሊየን ብር ማዳን ተችሏል።

በመንግስት በኩል ሊፈጸም ከነበረ ግዢ ብቻ 19 ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ማዳን ተችሏል ያሉት አቶ የሱፍ፤ ይህም የተደረገው ባሳለፍነው በጀት አመት በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ሳይሰጡ በተቀመጡ ንብረቶች ላይ የቁጥጥርና የምዝገባ ሥራ በመስራታችን ነው ብለዋል።

እንደ አቶ የሱፍ ገለጻ፣ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ተቋማችን ጣልቃ እየገባ በፋይናንስ ቢሮዎች በኩል ግዢ ሊፈጸም ነበር። ተቋማችን ባደረገው የቆጠራ ሥርዓት እነዚህ ንብረቶች በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ሥራ ፈተው መቀመጣቸውን ደርሰንበታል።

ላፕቶፖች፣ ኮምፒተሮች፣ ፕሪንተሮችና ሞተር ሳይክሎች ሊፈጸሙ የነበሩ ግዢዎች ናቸው ያሉት አቶ የሱፍ፤ እቃዎችን በመግዛትና በመጠገን፤ ትርፍ ካለበት ቦታ ወደ ጎደለበት በመውሰድ አላስፈላጊ ወጪ መከላከል ተችሏል ብለዋል። በዚህ የቁጥጥር ሥራችንም ወደ 45 ሞተር ሳይክሎችን ለሴክተር መስሪያ ቤቶችና ለከተማ ግብርና ማዋል መቻላቸውንም ተናግረዋል።

ተቋሙ በህንጻ ዘርፍና በንብረት ዘርፍ ያሉትን አጠቃላይ ንብረቶች ላይ የቁጥጥር፣ የምዝገባና የማስወገድ ሥራ ይሠራል ያሉት አቶ የሱፍ፣ በቀጣይ አመት ዘመናዊ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን በመዘርጋትና በማጠናከር የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፍትሃዊ ፣ ቀልጣፋ ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ውጤታማ እንዲሆን እንሰራለን ብለዋል።

በህንጻና በንብረት ቁጥጥር ዘርፍ የነበሩ ተግዳሮቶችን በመቅረፍና ሳይንሳዊ ሂደቶችን በመጠቀም አላስፈላጊ የሆኑ ግዢዎችንና የንብረት ውድመቶችን ለመከላከል ተቋማችን ቆርጦ ተነስቷል ሲሉም ዋና ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

ተቋማችን የመንግስት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ስርአት ተግባራዊነት ይከታተላል ያሉት አቶ የሱፍ፤ ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች፣ሰነዶች፣አሰራሩን ከሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጪ ግዥ ለመፈፀም ወይም ከተፈቀዱ የንብረት አወጋገድ ሥርዓቶችና ስልቶች ውጭ ንብረት ለማስወገድ የሚጥሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።



# "የዓባይ ግድብ የፍትሐዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቀም መርህ መገለጫ ነው"

-ካሳጃ ፍሊፕ
የኡጋንዳው መከረሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የዓባይ ግድብ የፍትሐዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቅም መርህ መገለጫ ነው ሲሉ የኡጋንዳው መከረሬ ዩኒቨርሲቲ ካሳጃ ፍሊፕ (ፕ/ር) ገለጹ። የተፋሰሱ አገራት የዓባይን ውሃ በምክንያታዊነትና ፍትሐዊነት ለመጠቀም ሊተባበሩና የጋራ ተጠቃሚነትን ሊያሰፍኑ እንደሚገባም ፕሮፌሰሩ አሳስበዋል።

በኡጋንዳው የመከረሬ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ህዝብ አስተዳደር ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ካሳጃ ፍሊፕ እንዳሉት፤ ቀደም ሲል በዓባይ ግድብ በመገኘት የመጎብኘት እድል በማግኘታቸው መደሰታቸውን ገልጸው፤ ከነበራቸው ግምት በላይ የገዘፈና አህጉራዊ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት መሆኑን አረጋግጫለሁ ብለዋል።

"ህዝብን በማስተባበር እንዲህ አይነት ፕሮጀክት መገንባት አስደናቂ ነው" ያሉት ፕሮፌሰር ካሳጃ የግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ የቀጣናውን የልማት ትሰስር በማጠናከር በኩል የላቀ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያና ኡጋንዳን ጨምሮ ለአካባቢው አገራት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር አሳላጭ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ የጥቁር ዓባይ መነሻ እንደሆነች ሁሉ ኡጋንዳም የነጭ ዓባይ መነሻ በመሆኗ በፍትሐዊ የውሃ አጠቃቀምና የጋራ ጠቀሜታ ያላቸውን ፕሮጀክቶች እውን በማድረግ አርአያነት ያለው ተግባር እየፈፀሙ መሆኑን ገልጸዋል።

የዓባይ ወንዝ ድንበር ተሻጋሪ ከሆኑ የአገራት የጋራ ሀብቶች አንዱ በመሆኑ፣ ምክንያታዊና ፍትሃዊ የውሃ ሀብት አጠቃቅም ስርዓትን ማስፈን ተገቢ ነው ብለዋል። በዚህ ረገድ የዓባይ ግድብ ለፍትሃዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቅም መርህ መገለጫ ፕሮጀክት እንደሆነ ተናግረዋል።

የዓባይ ውሃ ሃይል እያመነጨ ፍሰቱ ሳይገታ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ጠብቆ እየተጓዘ መሆኑን በጉብኝታችን አረጋግጠናል የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ የናይል ወንዝ ፍሰትን በተሳሳተ መልኩ የሚገልጹ መረጃዎች ፍፁም ከእውነታው ያፈነገጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በፕሮጀክቱ ጉዳይ ላይ የሚነሱ የድርድር ጉዳዮች የአፍሪካን ችግር በአፍሪካ የመፍታት ማዕቀፍ እልባት ሊበጅላቸው እንደሚገባ ገልፀው፤ ግድቡን ፖለቲካዊ መልክ መስጠት ተገቢ አይደለም ብለዋል።

በመሆኑም በግድቡ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ ከምዕራባዊያን መፍትሄ ይመጣል ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ እንደ አፍሪካ በውይይት መፍታት ይቻላል የሚል ጽኑ እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የውሃና መስኖ ሚኒስትር ከፍተኛ አማካሪ ሮበርት አሚኖ በበኩላቸው፤ የዓባይ ግድብ ፕሮጀክት ግሩም የምህንድስና ውጤት እንደሆነ ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያውያን የግድቡን ፕሮጀክት የመሩበትና የገነቡበት መንገድ ለሌሎች አገራትም ትልቅ ምሳሌ እንደሆነ መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የውሃን ሃብት በፍትሃዊና ምክንታዊ መርህ መጠቀም እንደሚገባ ገልጸው፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከኢትዮጵያ አልፎ ለቀጣናው የብርሃን አማራጭ የሚሆን የጋራ ፕሮጀክት በመሆኑ ሁሉም ሊደግፈው ይገባል ብለዋል።

# በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ81 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል

- ኩባንያው በአይሲቲ ፓርክ በ60 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ሊያካሂድ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ81ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል መፈጠሩንና ከ931 ሚሊዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በአይሲቲ ፓርክ ውስጥ 10 ሺህ ካሬ ሜትር የለማ መሬት በመከራየት 60 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኢንቨስትመንት ሊያካሂድ መሆኑ ተመልክቷል።

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በትናንትናው ዕለት የለማ መሬት የሊዝ ኪራይ የስምምነት መግባቢያ ሰነድና በጋራ መስራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳንዶካን ደበበ በፊርማ ስነስርዓቱ ላይ እንደተናገሩት፤በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከ125 በላይ የውጭና የሀገር ውስጥ አምራች ኩባንያዎች ገብተው እየሰሩ ነው ።ከ81ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎችም የስራ እድል ተፈጥሯል። እነዚህ ፓርኮችም ከ931 ሚሊዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ገቢ አስገኝተዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ340 ሚሊዮን በላይ ትርፍ ማስመዝገብ መቻሉን የገለጹት አቶ ሳንዱካን፤ መንግስት አቅም ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶችን በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የዲጂታል ኢኮኖሚ ኢትዮጵያ እውን እንዲሆን እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።




ይህን ምቹ ሁኔታ ተጠቅሞ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያም በአይሲቲ ፓርክ 10 ሺህ ካሬ ሜትር የለማ መሬት በሊዝ በመከራየት 60 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መዋዕለ ንዋይ ኢንቨስት እንደሚያደርግ አመልክተዋል።

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ በአይሲቲ ፓርክ የሚገነባው ዘመናዊ ዳታ ማዕከል የብሔራዊ የኮሙዩኒኬሽን አውታሮችን ሽፋንና ጥራት ማሻሻልና ማህበራዊ-ኢኮኖሚውን ማቀናጀት የዲጂታል ኢንዱስትሪን ማዘመን የዲጂታል ሽግግሩን እንደሚደግፍ ገልጸው፤ በመረጃ ማዕከል የፕሮጀክት አስተዳደርና አጠቃቀም ክህሎት ላይ ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች እና በተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ለሚሰሩ ሰራተኞች የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ እንደሚያግዝ አብራርተዋል።

በተጨማሪም በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰሩ ባለሃብቶች አስተማማኝ፣ ቀልጣፋና ምርቶቻቸውን በዲጂታላይዜሽን ሂደት እንዲደግፉ እንደሚረዳም አስገንዝበዋል።

የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈጻሚ አንዋር ሱሳ በበኩላቸው፤ ኩባንያቸው በቀጣይ ከኮርፖሬሽኑ ጋር እንደሚሰራ ገልጸው፤ ለተደረገላቸው ድጋፍ አመስግነዋል። ኩባንያው ኢትዮጵያ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ወደፊት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል አንዱ ይህ ኢንቨስትመንት መሆኑን ተናግረዋል።ይህም በኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት እንደሚያግዝም ገልጸዋል።

እንደ ዋና ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ የሚገነባው የመረጃ ማዕከል ቲር 3 ሲሆን ለዲጂታል ኢትዮጵያ ግንባታ መሰረት ይጥላል። የሚገነባው የመረጃ ማዕከል በዋናነት አገልግሎት የሚሰጠው ለሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ቢሆንም ለሌሎች ተቋማትም አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆኑን ጠቁመዋል። በፓርኩ ያለውን ነባሩን የመረጃ ማዕከል እንዲዘምን የሚያደርግ ግንባታ መሆኑን አመልክተዋል።

ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ በ850 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድርሻን በመግዛት ወደ ገበያ በመግባት በምስራቅና በሰሜኑ የአገራችን ክፍሎች አገልግሎት መስጠት የሚያስችለውን በአራት ከተሞች የኔትወርክ ሙከራ ጀምሯል። እስከ መጪው ሚያዝያ ወር 2015ዓ.ም ድረስ 25 ከተሞችን አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችለውን ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል።



ወ/ሮ ሀቢባ ሲራጅ



አቶ መክብብ ወልደሐና

## አዲስ አበባን ወረቀት አልባ አገልግሎት የሚሰጥባት ስማርት ሲቲ ለማድረግ እየተሰራ ነው

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባን ወረቀት አልባ አገልግሎት የሚሰጥባት ስማርት ሲቲ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እና የቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

ቢሮው ትናንት የ13 ዓመታት ጉዞውን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት የቢሮው ኃላፊ ወ/ሮ ሀቢባ ሲራጅ እንደተናገሩት፤ ከተማዋ ደህንነቷ የተጠበቀና ወረቀት አልባ አገልግሎት የሚሰጥባት እንድትሆን በሁሉም ክፍለ ከተሞች የኔትወርክ መሠረተ ልማት ዝርጋታ እየተከናወነ ነው።

ቢሮው በከተማ መስተዳድሩ ያሉት ተቋማት በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ ሶፍትዌሮች እየበለፀጉ መሆኑን የተናገሩት ወ/ሮ ሀቢባ፤ መድረኩ ያስፈለገበት ዓላማ የለሙና ሙሉ በሙሉ ወደሥራ ገብተው አገልግሎት ላይ ያሉ፣ ሲስተማቸው የተቋረጠና ጭራሽ ወደ ሥራ ያልገቡ ሶፍትዌሮችን ወደ ሥራ በማስገባት ውጤታማ የሚሆኑበት ሁኔታ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር መመካከር ታስቦ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ቢሮው የመረጃ ደህንነት ለማረጋገጥ ውስብስብ የሆኑ ሶፎትዌሮችና ሲስተሞችን እንደ ኢንፎርሜሽንና መረጃ ደህንነት ያሉ የፌዴራል ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን የገለጹት ኃላፊዋ፣ ባለፈው ዓመት በዘጠኝ ቢሮዎች ላይ የተጀመረው የወረቀት አልባ አገልግሎት አፈጻጸም 50 በመቶ ላይ መሆኑንና በቀጣይ ለክልሎች ምሳሌ በሚሆን መልኩ በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመዋል፡፡

ምክትል ቢሮ ኃላፊው አቶ መክብብ ወልደሐና በበኩላቸው፣ እስካሁን በመዲናይቱ በስምንት ክፍለ ከተሞች በተለያዩ የመንግስት ተቋማት በ1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ማከናወናቸውንና 16 ሶፍትዌሮች ማበልፀግ መቻላቸውን አመልክተዋል።

በውስጥ አቅም በመታገዝም 149 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግስት ወጪ ማዳን እንደተቻለ ገልፀው፤ ጠንካራ ጎናቸውን በማጎልበት ድክመታቸውንም በማረም በ2022 ዓ.ም መዲናይቱን ሙሉ በሙሉ ስማርት ሲቲ ለማድረግ እየሰሩ መሆናቸው አስታውቀዋል።

በከተማ መስተዳድሩ በስምንት ክፍለ ከተሞችና በ114 ወረዳዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የኔትዎርክ ዝርጋታ መጠናቀቁንና በተመሳሳይ መልኩ በለሚ ኩራና በልደታ ክፍለ ከተሞች ደግሞ ዝርጋታው በቀጣይ ጊዜያት እንደሚከናወን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በትምህርት ዘርፍም በተገነቡ 39 ትምህርት ቤቶች የስኩልኔት ሲስተም መዘርጋቱን አንስተዋል፡፡

ከደህንነት ካሜራዎች፣ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃ፣የተቀናጀ የመሬት አስተዳደር፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት እና ሌሎችም በብዛት በቢሮው መሰራቱን የተናገሩት አቶ መክብብ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርም የተገኘው እውቀት ከከተማው አልፎ ለአገሪቱ ቴክኖሎጂና ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

## በቀጣዮቹ ቀናት የምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋ የዝናብ ሁኔታ ይኖራቸዋል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በመስከረም ወር ከሰሜን ምሥራቅ እና ምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ውጪ ባለፉት አስር ተከታታይ ቀናት ውስጥ የተስፋፋው የዝናብ ስርጭት እንደሚቀጥል የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ አጠቃላይ የዝናብ መጠን ከምሥራቁ ሀገሪቱ ክፍሎች ጀምሮ እየቀነሰ እንደሚሄድ ተገልጿል ፡፡

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሜትሮሎጂ ትንበያ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ምርምር መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር አሳምነው ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመስከረም ወር ውስጥ የተስፋፋ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ከሰሜን ምሥራቅ አንጻራዊ በሆነ መልኩ እየቀነሰ መሆኑን የሜትሮሎጂ መረጃዎችን በመጥቀስ አመላክተዋል፡፡

የዘነበው ዝናብ ከመደበኛ ዝናብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በትግራይ፣ በአማራ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ደቡብ አፋር አዋሽ አርባ አካባቢ፣ በጋምቤላ፣ ቄለምና ምዕራብ ወለጋ ሆሮ ጉዱሩና ምስራቅ ወለጋ ፣ በጅማ ቡኖ በደሌ ሰሜን ሸዋ በሁሉም ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡

በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች በአማራ አካባቢዎች ምዕራብ እና መካከለኛ አሮሚያ ፣በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ደቡብ ደጋማ አካባቢዎችን ጨምሮ የተስፋፋና ጠንካራ የደመና ክምችት እንደነበራቸው ገልጸዋል፡፡

ባሳለፍነው አስር ቀናት በ24 ሠዓት ውስጥ ጋምቤላ አቦቦ 40ሚ.ሊ፣ ምዕራብ አሮሚያ በደሌ 43 ሚ.ሜ፣በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች በቡኢ 53 ሚ.ሜ ፣በጎሬ በተከታታይ ቀናት 42 ሚ.ሜ፣ በአማራ ቻግን 43 ሚ.ሜ፣ድሬዳዋ 40 ሚ.ሜ ግንር 80 ሚ.ሜ ፣ካችሴ 45 ሚ.ሜ ፣ ልሙ ገነት 88ሚ.ሜ፣ መተሃራ 69ሚ.ሜ፣ በአዳማ 45 ሚ.ሜ፣ በአማን 54 ሚ.ሜ በተርጫ 48 ሚ.ሜ፣ ላሬ 88 የዝናብ መጠን መመዝገቡን ገልጸዋል፡፡

የዘነበው ዝናብ መጠን በክልል እና በሀገር ደረጃ ሲታይ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከ25 ሚ.ሊ. እስከ 169 ሚ.ሜ ሲሆን በአማካይ በተለያዩ አካባቢዎች ከአራት እስከ ዘጠኝ ቀናት ዝናብ ያሳያል፡፡



ዶክተር አሳምነው ተሾመ

የክረምትን አየር ድንበር መሰረት በማድረግ የቀጣይ የመስከረም ወር አየር ሁኔታ ትንበያን ገልጸዋል፡፡ መስከረም የክረምት ወቅት መውጫ እንደመሆኑ አሁን ባለው ሁኔታ ከሰሜን ምስራቅ አማራ አካባቢ፣ አፋር ፣ ከምስራቅ ሀገሪቱ ክፍሎች እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ወደ መካከለኛው እና ምዕራብ ሀገሪቱ ክፍሎች ቀስ በቀስ እየጨመረ የሚሄድበት ሁኔታዎች እንደሚኖራቸው ጠቅሰው፤ በምዕራብ አጋማሽ እና ደቡብ ምዕራብ ሀገሪቱ ክፍሎች ጥሩ የዝናብ ስርጭት ይኖራቸዋል ፡፡

አልፎ አልፎ ከሚከሰተው ፀሐይ መጠን በመነሳት በአንዳንድ ሀገሪቱ ክፍሎች በምዕራብ በጅማ ፣ ኢሉ አባቦር ቡኖ በደሌ፣ በአማራ ክልል ባህርዳር አካባቢ ፣ በሰሜን ሸዋ ዞኖች ከባድ የዝናብ መጠን እንደሚጠበቅ ትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ ፡፡

በሚቀጥሉት ቀናት ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሀገሪቱ ክፍሎች ለዝናብ መፈጠር አመች የሆነ የአየር ሁኔታዎች ክስተቶች ስለሚኖሩ ጥሩ የዝናብ ስርጭት ይኖራቸዋል ፡፡

በአሁኑ ወቅት ያለው የአየር ሁኔታ ለግብርናው ዘርፍ ፣ ለውሃ ስራ፣ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በቂ ውሃ ማስገኘት የሚያስችል የዝናብ ስርጭት መኖሩን ጠቁመው፤ በአንዳንድ ቦታዎች ውሃ አዝርዕት ላይ በመተኛት በሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ኅብረተሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት መክረዋል፡፡ ኅብረተሰቡ የግብርና ባለሙያዎችን ምክር በመቀበል አደጋ እንዲከላከሉ ጥሪ አቅርበው በአጠቃላይ አስጊ የሚሆኑ ክስተቶች እንደማይጠበቁም አያይዘው ገልጸዋል፡፡

የክረምት መጨረሻን ተከትሎ የሚገባውን የ2015 ዓ.ም በጋ አየር ሁኔታ ከጥቅምት እስከ ጥር ያለውን ሁኔታ በቅርቡ ለሕብረተሰቡ ይፋ ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ እየሰራበት መሆኑን አያይዘው ገልጸዋል፡፡

# ኮሚሽኑ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በ2015 በጀት ዓመት 1 ነጥብ 12 ሚሊየን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ኡመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ኮሚሽኑ በ2015 በጀት ዓመት በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት 1 ነጥብ 12 ሚሊየን ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ ነው።

በኅብረት ሥራ ማህበራት ካለፈው ዓመት ከተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በላቀ መልኩ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንደሚሠራ የገለፁት አቶ አብዲ፤ ከዘህ ውስጥ 40 ሺህ ያህሉን በቋሚነት እና 1 ነጥብ 08 ሚሊየን ያህሉን ደግሞ በጊዜያዊ የሥራ ዕድል ሥራ ለመፍጠር መታቀዱን አብራርተዋል።

በኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ይፈጠራሉ ከተባሉ የሥራ ዕድሎች በርካቶቹ በጊዚያዊነት የሚፈጠሩ ቢሆንም ለሃገር ኢኮኖሚ ቀላል የማይባል ፋይዳ እንዳላቸው የጠቀሱት አቶ አብዲ፤ በተለይ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች የራሳቸውን ሥራ ለመሥራት ልምድ ቀስመው የሚወጡባቸው እንደሆኑ ጠቁመዋል።

የሥራ ዕድሉ በአጠቃላይ በኅብረት ሥራ ማህበራት የሚፈጠር ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ የሥራ ዕድሎቹ የሚፈጠሩት በኅብረት ሥራ ማህበራት በሚገኙ የተለያዩ ዘርፎች መሆኑን ጠቅሰዋል።

በኅብረት ሥራ ማህበራቱ ይፈጠራሉ የተባሉት የሥራ ዕድሎች በዘርፍ ሲታዩም በማምረትና በአገልግሎት የሥራ ዓይነቶች ላይ፤ ብድር በወሰዱ አባላት በሚፈጠር የሥራ ዕድል፤ ዕሴት በመጨመር የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት በሚፈጠር ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ ዕድል እና በሜካናይዜሽንና ሌሎች አገልግሎቶች በሚፈጠር የሥራ ዕድል መሆናቸውንም አብራርተዋል።

እያንዳንዱ ዘርፍ ላይም በቁጥር የተለዩ የሥራ ዕድሎች እንደሚፈጠሩ እና ከባለፈው ዓመት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር እንደሚሠራ ምክትል ኮሚሽነሩ አብራርተዋል።

በማምረትና በአገልግሎት የሥራ ዓይነቶች ላይ ከ22 ሺህ በላይ ብድር በወሰዱ አባላት በሚፈጠር የሥራ ዕድል 700 ሺህ በላይ፤ ዕሴት በመጨመር የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት በሚፈጠር ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ ዕድል ከ300 ሺህ በላይ እና በሜካናይዜሽን ሌሎች ዘርፎች ከ33 ሺህ በላይ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ነው የተናገሩት።

በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ በኅብረት ሥራ ማህበራት ከ844 ሺህ በላይ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር መቻሉንና ይህም ታቅዶ ከነበረው ከ550 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ከ100 በመቶ በላይ አፈፃፀም መመዝገቡን ምክትል ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

## ‹‹የቡና ሀብታችን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በ10 አመቱ የልማት ግቦች ውስጥ ለግብርና በተሰጠው ትኩረት የአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮችን ኑሮ እየለወጠ ይገኛል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የግሉ ዘርፍ እንዲስፋፋ ማድረግ ለአገር እድገት ትልቅ በር የሚከፍት እንደሆነም ጠቁመዋል።

ለብዙ ዘመናት የግል ዘርፉ እንዳያድግ ተደርጎ መቆየቱን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቷ፤ ሆኖም ያለ ግል ዘርፉ ተሳትፎ የአገር እድገት ስለማይኖር ዘርፉን መደገፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ ቡና ጎረቤትን ከጎረቤት፣ አገርን ከአገራት የሚያገናኝ በመሆኑ ጥቅሙ ምርትን ከማሳደግ ያለፈ ነው። በዚህ አመት ከተገኘው የውጭ ምንዛሬ 72 በመቶ የሚሸፍነው የግብርና ዘርፍ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 35 በመቶ የሚሆነው የቡና ምርት ነው። ስለሆነም ከከፍተኛ አመራሩ እስከ ታችኛው የአመራር እርከን የቡና ዘርፉን በቅርበት በመከታተል ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን በእውቅና ስነስርአቱ ላይ እንዳሉት፣ በ2014 እንደአገር የገጠሙንን ችግሮች በመቋቋም በግብርና፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በቡናና በበጋ መስኖ አኩሪና የልማት ድሎች ተመዝግበዋል።

እንደ አገር የተመረጡ 10 አገራዊ የልማት ፕሮግራሞች ውስጥ የግብርናው ዘርፍ ጉልህ ሚና እንዳለው የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ምርቶችን ማሳደግ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት፣ የስራ ዕድል ፈጠራ ወሳኝ የልማት መስኮች ናቸው ብለዋል።

ቡና አልሚ አርሶ አደሮች የድካማቸውን ገቢ ማግኘት እንዲችሉ የተራዘመ የግብይት ሰንሰለትን በማሳጠር የተሻለ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በቀጣይም የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የቡና ዝርያን ማራባት፣ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚያስችሉ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ በመርሃግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የቡናን ገቢ ለማሳደግ አሰራሮችንና ደንበኞችን በማሻሻል ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል። ለአብነትም ከ470 ሺ ሄክታር በላይ የቡና ማሳያዎች እንዲታደሱ ተደርጓል። የቡና ስርዓተ ትምህርት በመቅረጽ፣ የቡና ቅምሻ ማእከል በማቋቋም የቡና እሴትን ለመጨመር ተሰርቷል።

ዳይሬክተሩ፣ አለም የኢትዮጵያን ቡና ለመግዛት ጉጉት እያሳየ ነው፤ ስለሆነም ጠንክሮ መስራት አስፈላጊ ነው። ለአብነትም «በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ» ውድድር አንድ ኪሎ ቡና 47 ሺ ብር የተሸጠበት ለቀጣይ ስራ የሚያነሳሳ ነው። ሽልማቱ ጥሬ ቡና በመላክ ፣ በተሻለ ዋጋ ጥሬ ቡና የሸጡ ፣ ከፍተኛ ገቢ ያስገኙ ሴት የቡና ላኪዎች፣ ዕሴት የተጨመረበት ቡና በመላክ ከፍተኛ ገቢ ያስገኙ ላኪዎችን ያካተተ ነው ብለዋል።

ከፍተኛ ገቢ ያስገኙ አምራች አርሶ አደር ላኪዎች፣ ገበሬዎች፣ ቡና ህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ የቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪዎች በአጠቃላይ 267 ባለድርሻ አካላት ከኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እውቅና ተበርክቶላቸዋል። በሻይ እና ቅመማ ቅመም ዘርፍ የተሻለ አፈጻጸም የነበራቸው ግለሰቦችና ድርጅቶችም እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ በዘንድሮው የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ 2022 ውድድር በጥራቱ በአንደኝነት ከፍተኛ ነጥብ ያመጣውና በአለም አቀፍ የበይነ መረብ ጨረታ አንዱ ኪሎ በ884 ዶላር የተሸጠው ቡና ቅምሻ ተደርጓል።

በ2014 በጀት አመት ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘርፉ 1 ነጥብ 4 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘቷ የሚታወስ ነው።

## “አሸባሪው ትህነግ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ቡድኑ ሴራን፣ ማደናገርና የሀሰት ፕሮፓጋንዳን ባህሉ አድርጎታል ያሉት ተመራማሪው፤ ከዚህ በፊት የመንግስት የተናጠል የተኩስ አቁም ስምምነትን ማጣጣልና በሌላ በኩል ደግሞ ወደ መሀል አገር እየገሰገስን ነው የሚል የውሸት መረጃ ሲያሰራጭ እንደነበር ጠቅሰዋል።

በአፍሪካው አህጉር ውስጥ የማይኖር እስኪመስል ድረስ የአፍሪካ ህብረትን አንቋሾ ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልፅ እንደነበር የገለጹት አቶ ሱራፌል፤ በአፍሪካ ሕብረት ሲመራ የነበረውን የሰላም ጥሪት አልተቀበለም፤ የአፍሪካ ሕብረትን ሲያንቋሽሽና ተአማኒነት እንዳይኖረው ሲያደርግ ነበር ብለዋል። አሁንም ቢሆን አገርን የማፍረስ ተልዕኮ ተቀብሎ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ተናግረዋል።

ለሰላም ቁርጠኛ ከሆነ ራሱን እንደ አንድ ሉአላዊ አገር መመልከቱን ትቶ ራሱን ለፌዴራሉ መንግስት ማስገዛት፤ በየጊዜው ተቀያያሪ ሀሳቡንና ማደናገሩን ወደ ጎን በማለት በገፍ የጦር መሳርያ ያስታጠቃቸውን ሃይሎች ትጥቅ ማስፈታት እንዲሁም ከመንግስት ጋር ያለውን የፖለቲካ ልዩነት በሰላማዊ መንገድ መፍታት አለበት ብለዋል።

አቶ ሱራፌል እንዳሉት፤ ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ያስፈልጋል ካለ በመጀመሪያ ትጥቅ መፍታት አለበት ፣ በመቀጠል ብዙ ታዛቢዎች ባሉበት የፖለቲካ ልዩነቱን በድርድር መፍታት ይችላል። በአንጻሩ በየጊዜው በውሸት በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ሰላም ፈላጊ መስሎ ለመታየትና እርዳታ ለማግኘት አስቦ ከመንቀሳቀስ መታቀብ አለበት።

በትግራይ ክልል ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰው የነፍስ ወከፍና የቡድን የጦር መሳሪያ የታጠቀ በመሆኑ አለም አቀፍ ተቋማትም የሽብር ቡድኑ ትጥቅ ፈትቶ ወደ ሰላማዊ ሁኔታ እንዲመለስ መንግስትን መደገፍ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን በቀጣይ ሌላ ችግር እንደሚፈጥሩና የትግራይ ሕዝብም የባሰ ችግር ውስጥ እንደሚገባ ገልጸዋል።

## “አሸባሪው ትህነግ በድብቅ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ቡድኑ ከባድ ምት ሲደርስበት ለሰላም የቆመ በመምሰል አለምን ለማደናበር ሙከራ ያደርጋል ያሉት አቶ አንዳርጋቸው፤ ከዚህ ውጭ ግን ለሰላም ምንም አይነት ፍላጎት የሌለው ቡድን መሆኑን በተደጋጋሚ ካደረጋቸው ጥፋቶች እና ካመከናቸው የሰላም እድሎች መገንዘብ እንደሚቻል ነው ያስረዱት።

በቅርቡም የሽብር ቡድኑ ያለና የሌለውን ሀይል በማሰባሰብ በድብቅ ባስገባው የጦር መሳሪያ በመተማመን የከፈተው ሦስተኛ ዙር ጦርነት እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ ከባድ ኪሳራ እየደረሰበት በመሆኑ ለሰላም የቆመ ለመምሰል እየጣረ መሆኑን ጠቁመዋል። ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ለመወሰን ወሳኝ ምዕራፍ ላይ መሆናቸውን በደንብ ማጤን አለባቸው።

አሸባሪው ትህነግ በርካታ የጦር መሳሪያዎችን ከውጭ በድብቅ እንዳስገባ በቂ መረጃዎች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ አንዳርጋቸው፤ ነገር ግን እሱ እንዳሰበው ድል በጦር መሳሪያ ብቻ ስለማይገኝ በሁሉም አቅጣጫ ባስተናገደው ከባድ ምት የተመካበት ጦር መሳሪያ ከንቱ መሆኑን በመገንዘብ ለሌላ ጦርነት ራሱን እንደገና ለማደራጀት ጊዜ ለመግዛት እየሞከረ እንደሆነ ነው የገለጹት።

እንደ አቶ አንዳርጋቸው ማብራሪያ፣ ትህነግ በተጠና መልኩ እንደ ልቡ የሚያቀርባቸው የጦርነትና የሰላም አማራጮች በተራዘሙ ቁጥር አደጋ አላቸው። ጦርነት በተራዘመ ቁጥር የህብት ብክነት፣ የተዋጊ ሀይሎች መሰላቸት አልፎ ተርፎም በህዝቡ ዘንድ ቅሬታ ሊፈጥር ይችላል።

በተጨማሪም በአሸባሪው ትህነግ መንግስት በየዓመቱ ሙሉ ትኩረቱን ጦርነት ላይ አድርጎ ኑሮ ውድነቱ፣ ሌብነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲባባሱ ያለውን አቅም ሁሉ አሟጦ እየሰራ ነው። በመሆኑም ችግሩን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቅረፍ የሀይል እርምጃ ብቸኛው አማራጭ ሆኖ ቡድኑን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከዚህ ድርጊቱ ማስቆም ይገባል።

የአሸባሪው ትህነግ ጉዳይ እንደ ቀላል የሚታይ ጉዳይ ሳይሆን ከኋላው ያለው መዘዝ የአገሪቱን ህልውና በእጅጉ የሚፈታትን መሆኑን የጠቆሙት አቶ አንዳርጋቸው፤ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የቀይ ባህር ቀጣናን በቀላሉ ለመቆጣጠር እንዲመቻቸው ቡድኑን እንደገና ለማንገስ እየፈጠሩ ካለው ጫና ለመገላገል ጨከን በማለት ለአፍሪካውያን አስተማሪ የሚሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ብለዋል።

ጦርነቱ ሳይቋጭ በእንዲህ ከቀጠለ ምዕራባውያን አሸባሪውን ቡድን ወደፊት ለማስፈንጠር አሁን ከሚያደርጉት የእርዳታ መከልከልና የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነት አልፎ የአገሪቱ ገንዘብ ላይ ጫና ፈጥረው ኢኮኖሚውን ለማዳከም የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ ሀይሎች በእሳት እየተፈተነች መሆኗን በመገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ ሕዝብ ጸንቶ ለመቆም ቀበቶአቸውን በደንብ ማጥበቅ ያስፈልጋል ያሉት ፖለቲከኛው፣ መንግስት ስለፈለገ ብቻ ሰላም ስለማይመጣ አስፈላጊውን መስዋእትነት ሁሉ በመክፈል የሽብር ቡድኑን አደብ ከማስያዝ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደማይታያቸው ተናግረዋል።

መንግስት በትህነግ ሳቢያ በተለያየ መልኩ በሕዝብና በአገር ላይ የተደቀነውን አደጋ ለመቀልበስ በአንድ በኩል መዋቅሩን በማጠናከር ለህዝብ በማድረስ በሌላ በኩል ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከሁሉም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በቅርበት እንዲሰራም መክረዋል።

## “የማህበራዊ ሚዲያዎችን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ስንጀምር የአንድነትና የሰላም ግንባታ ስራዎች ላይ የሚያሳድሩትን ጫናና ጠቀሜታን መለየት እንችላለንም ብለዋል፡፡

አብዛኞቹ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ለዜጋም ሆነ ለሀገር ጠቃሚ መረጃዎችን ለይተው አይለቁም ያሉት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፤ በመሆኑም ዜጎች የማህበራዊ ሚዲያዎችን መረጃ ሲጠቀሙ በቅድሚያ ተገቢነቱን የማየት ልምድ ሊኖራው ይገባል ብለዋል፡፡

ይህን ካላደረግን ሀቁን ጥለው፣ በቃላት ለዛ አንቆለጳጽሰው ልማታችንን ለማደናቀፍ፣ ሰላማችንን ለመንሳት ፣ ከድህነት እንዳንወጣ አርቀው ለመቅበር ሴራ በሚጎነጉኑልን አካላት እጅ እንወድቃለን ሲሉ መክረዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አክለውም፣ ይህ ከመሆኑ በፊት መረጃዎችን እውነታ ካለው፣ ከትክክለኛ ምንጮች ልንወስድና ልንጠቀም ይገባናል ብለዋል፡፡

ሼህ ሐጂ ኢብራሂም እንዳሉት፤ አብዛኞቹ የማህበራዊ ሚዲያዎች መረጃዎችን ከትክክለኛ ምንጭ ሳያጣሩ የሚያሰራጩና የሚዘግቡ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ማለት አይቻለም፣ በመካከላቸው ለሀገራዊ ልማት መሳለጥ የሚሰሩ አሉ፣ እነሱን መለየት፣ ማበረታታት ይገባል ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል፡፡

ከበዙት የማህበራዊ ሚዲያዎች መካከል ለማህበረሰቡን እየጠቀሙ ያሉ መኖራቸውን ያወሱት ፕሬዚዳንቱ፣ ማህበረሰቡ መረጃን ከትክክለኛና ተጠያቂነት ካላቸው የመረጃ ምንጮችና ማህበራዊ ሚዲያዎች ሊወስድና ሊጠቀም ይገባል ብለዋል፡፡

ለትክክለኛ የሀገር ግንባታና ሰላም መስፈን የሚሰሩ ሚዲያዎች መኖራቸውን የጠቆሙት ሼህ ሐጂ ኢብራሒም፤ ለመረጃ ምንጭነት የምንወስዳቸውን የማህበራዊ ሚዲያዎች መረጃ ከነባራዊውና ሀገራዊው ሁኔታ ጋር እያገናዘብን መሆን እንዳለበት አስገንዝዋል፡፡

የጥፋት ተልዕኮ ያላቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች ሀገርን በማፍረስ፣ ማህበረሰብን በማሳሳትና ልማትን በማደናቀፍ የተጠመዱ ናቸው፡፡ አዛገ‍ፓቻቸው የሚከፍሏቸው ባሳሳቱት፣ ባፈራረሱት፣ ባበጣበጡት፣ ባለያዩት ልክ ነው፡፡ ከእነዚህ ዓይነቶቹ የመረጃ ምንጮች መራቅ ያስፈልገናል ብለዋል፡፡

እንዲህ አይነት ሚዲያዎች የተመሰረቱት ለአንድ አካል የጥፋት መሳሪያነት ነው፤ በሀገር ሰላምና ልማት እንዲሁም በዜጎች ላይ ለሚደርስ ችግር ለአፍታም አያስቡም ሲሉም አክለው ተናግረዋል፡፡

ሼህ ሐጂ ኢብራሒም፣ አሁን ያለፈውን ወደጎን ትተን ለወደፊት በጋራ መቆምና መስራት ያስፈልገናል፣ በጋራ ቆመን ልማታችንና ሰላማችንን ማስቀጠል ይጠበቅብናል ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም ፈላጊነት ከኃይል አምልኮና ከእብሪት ነጻ መሆንን ይጠይቃል!

በሰላም እጦት የተነሳ ለአያሌ ዓመታት በኢትዮጵያ ብዙ ዜጎቹ ህይወታቸውን አጥተዋል፣ የዜጎችና የሀገር ሀብት ክፉኛ ወድሟል፤ የሀገር ገጽታ ጎድፏል ከዚህም የተነሳ የሰላምን ዋጋ የቱን ያህል ውድ እንደሆነ ከማንም በላይ ጠንቅቃ ትረዳለች። ስለ ሰላም ሲባልም ውድ ዋጋ ተከፍሏል።

ስለሰላም ሲዘመርም ሆነ ስለ ሰላም ያለው ቁርጠኝነት ሲገለፅ ዋነኛ ዓላማው ሰላም ምንያህል ውድ እንደሆነ ለማሳየትና ሰላምን ለማምጣት ነው። በሰላም ጉዳይ ለይስሙላ ተብሎ የሚያደርግ ነገርም አይኖርም። ሰላም ሀገራችን ለጀመረችው የልማትና የብልጽግና ጉዞ አልፋና ኦሜጋ ነው። ሀገርና ትውልድን ወደ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ለማሻገር ለተጀመረው ጉዞም መተኪያ የሌለው ወሳኝ አቅም ነው።

የሰላም እጦት ሀገር እያመሰ፣ የንጹኃን ዜጎችን ህይወት እየቀጠፈ፣ ሀብትና ንብረትን እያወደመ ፣ የሀገር ገጽታን በእጅጉ እያጠለሸ በህዝብ ይሁንታ ወደ ስልጣን የመጣ መንግስት ስለ ሰላም ደንታ ቢስ ይሆናል ብሎ ማሰብ ሌላ ተልእኮ ከሌለው በስተቀር ከጤነኛ አእምሮ የሚመነጭ ሃሳብ አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም።

መንግስት የትኛውንም አለመግባባት ለዘለቄታው ለመፍታት ዋነኛው መንገድ መነጋገር መሆኑን በጽኑ አምኖ ራሱን በመነጋገር ለሚገኝ ሰላም ተገዥ ካደረገ ውሎ አድሯል። ለዚህ ሲልም በጦርነት መሀል ሳይቀር ብዙ ዋጋ ከፍሏል፤ እየከፈለም ነው።

መንግስት ዘላቂ ሰላም በውጊያ ቀጣና በሚገኝ ድል ብቻ እንደማይጸና በአደባባይ ከመግለጽ ጀምሮ በተጨባጭ በተግባር አሳይቷል። አሸባሪው ትህነግ በሕዝብ ግፊት ከስልጣን ተባሮ ትግራይ ላይ መሽጎ ወታደራዊ ሰልፍ በሚያሳይባቸው ወቅቶች መንግስት በሰከነ አዕምሮ ስለሰላም በሀገር ወግ መሰረት የሀገር ሽማግሌዎች፤ እናቶችን ጨምሮ አምባሳደሮች እንዲሸመግሉ ሞክሯል።

ወደ ጦርነትም የገባው ሁሉም ለሰላም የተዘረጉ እጆች ተገፍተው ሰሜን እዝ ላይ ክህደት ሲፈጸም ነው። መንግስት ያን ሁሉ ጥረት ሲያደርግ ህዝቡ የህግ የበላይነትን እንዲያስከብር አጥብቆ ይጠይቅ ነበር። ስለሰላም ሲባል በተደረገ ትዕግስትም ደካማ መንግስት አድርገው የቆጠሩትም ነበሩ። ጉዳዩ ግን የሰላምን ወድነትን የማይተካ ዋጋ ከመገንዘብ የመነጨ ነበር።

በህግ ማስከበር ዘመቻው መከላከያ በከፍተኛ ድል ላይ በነበረበት ወቅት የተናጠል የተኩስ አቁም በማድረግ ትግራይን ለቆ እንዲወጣ ያደረገው ለሰላማዊ አማራጭ ለመስጠት ብሎ ነው። ይህ የሰላም ጥረቱ ፍሬያማ ባይሆንም እንደ መንግስት ግን ማድረግ ያለበትን አድርጓል። በህልውና ዘመቻው ማግስትም እንዲሁ በህግ ጥላ ስር የሚገኙ የአሸባሪው ትህነግ ከፍተኛ አመራሮችን ከእስር የፈታውም ለሰላም ባለው ቁርጠኝነት ነው። ይህ ለምን ሆነ የሚሉ ጥያቄዎችም አደባባይ የሞሉበት ሁኔታ መከሰቱና ቅሬታ ፈጥሮ እንደነበርም የሚታወስ ነው።

ይሁንና ከዚሁ በተጻራሪው አሸባሪው ትህነግ የሰላም ጸር ሆኖና ሰላምን ለእኩይ ዓላማ ጊዜ መግዣ ለማድረግ ሲጥር ደጋግመን አስተውለናል። አሁን ትህነግ እያደረገ እንዳለው ሰላም የሰላም መግለጫ በማውጣትና ስለ ሰላም ማውራት ብቻውን የተፈለገውን ውጤት አያመጣም። ለሰላማዊ ንግግር ቅድመ ሁኔታዎችን መደርደርም የሰላም ጥረቶችን ከማሰናከል ባለፈ ምንም አይነት ፋይዳ አይኖረውም።

ግጭት እየቀሰቀሱና እያስቀሰቀሱ፣ ጦርነት እየከፈቱና እያቀጣጠሉ ስለሰላም ማውራትም የትም አያደርስም። ከሁሉም በላይ ስለሰላም ሲባል የሚከፈል ዋጋ መኖሩን በአግባቡ መገንዘብ እና ለዚህ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ወሳኝ ነው።

ሰላም የማምጣት ጥረት በቅድሚያ የልብ ዝግጁነትና ጽናትን፤ ከኃይል አምልኮና ከዚሁ ከሚመነጭ እብሪት መውጣትን ይፈልጋል። በሰላም እጦት በሕዝብና በሀገር ላይ የደረሱ ጥፋቶች አይቶ መጸጸትን፤ዳግም እንዳይከሰቱ ከራስ ጋር ቃል መግባትንም አጥብቆ ይሻል። ለዚህ ዋጋ መክፈል፤ ለዚህ የሚሆን መታመን፤ ለዚህ የሚሆን ስብእና ማበልጸግንም አብዝቶ ይፈልጋል።

ሰላማዊ አማራጭ አይደለም ለይስሙላ፤ ከልብ ተይዞም መፈጸም ከፍተኛ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው። ለዚህም ነው መንግስት ይህን ኃላፊነት በተጨባጭ እየተወጣ ያለው። የተከፈተበትን ሦስተኛ ዙር ጦርነት እየመከተም ለሰላማዊ አማራጭ የዘረጋውን እጅ አልሰበሰበም።ይህ ዛሬም ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ የሚያሳይ ነው።

በቅርቡ ከአሸባሪው ሕወሓት መንደር አፈንግጦ የወጣው ሰነድ እንዳመለከተው፤ አሸባሪው ትህነግ ሰላምን ለይስሙላና ለማታለያ እየተጠቀመበት ስለመሆኑ ፍንትው አድርጎ አሳይቷል። ከዚህም በላቀ አሸባሪው ትህነግ እየፈጸማቸው ያሉ ተግባራት ምን ያህል የሰላም ጸር እንደሆነ ያመላክታሉ።

በአጠቃላይ ሰላም ተግባርን የሚጠይቅ ተግባር እንደመሆኑ በውሸት ሊሸፈን ፈጽሞ አይቻልምና አሸባሪው ትህነግ ከዚህ የድብብቆሽ ጨዋታ ሊታቀብና አሁንም ሳይመሽበት ወደትክክለኛው መንገድ ሊመለስ ይገባል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የተጋረዱብን ሰሞነኛ ስኬቶች

ግርማ መንግሥቴ

እርግጥ ነው በችግር ተተብትበናል። «ሳይቸግር የጤፍ ብድር» እንዲሉ ራሳችን በራሳችን፤ እርስ በእርሳችን እየተበላላን ነው። አስታራቂው ጠፍቶ፣ የእብድ ገላጋዩ በዝቶ «እነሆ ...» እንደ ተባለው እነሆ ከጦርነት ወደ ጦርነት እየተሸጋገርን፤ ዙር እየቆጠርን ... በለው ... በለው ... እየተባባልን እንገኛለን። «ወንድም በወንድሙ ላይ ...» የተባለውን ቀድመን ተግባራዊ ለማድረግ ሽብ ረብ ላይ ነን። ይሁን እንጂ ... በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ብርሃን አለ።

«የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ »... እንዳለችው ሴትዮ ልክ ነው ብለን የተነሳንበትን ያረጀም ይሁን ያፈጀ ሀሳብ አውርዶ መጣል እንደ'ኛ የሚከብደው የዓለም ክፍል ያለ አይመስለኝም። ትናንትም፣ ዛሬም .... እዛው ... ከትናንትና ወዲያ የነበርንበት ቦታ ነው ያለነው። እሚያስፈራው እሱ አይደለም፤

እሚያስፈራው ነገም እዛው ከትናንት በስቲያ እነበርንበት ቦታ ላይ እንዳንሆን ነው። እሚያስፈራው ተነገ ወዲያም ከትናንት ወዲያን አልፈን እዛኛው «ወዲያ» ላይ ሆነን በብሔር እንዳንደራጅ ነው። ተደራጅተንም እንደ ገና «በለው ...»፣ «በለው ...» እንዳንባባል ነው። ያኔ ዓለም ጭራሹን ጥሎን እብስ ይላልና - ግልግል ነው።

የዚህ ጽሑፍ አላማ ባለንበት ጭለማ ውስጥ ብርሃንም መኖሩን መግለፅ ነው። መግለጽ ብቻም ሳይሆን ከተቻለ ማሳየትም ይሆናል። የዚህ መነሻው ደግሞ ያለንበት ጭለማ ብርሃኑን እንዳናይ፤ አይተንም እንዳናጣጥም እያደረገን መሆኑ እየታየ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ነው (ተስፋ ያለን መሆናችንን ለመጠቆም ያህል) ርዕሳችንን «የተጋረዱብን ሰሞነኛ ስኬቶች» በማለት ሰይመን ወደ «ሥራ» የገባነው። ከቡና እንጀምር።

ሰሞኑን ዓለም «ኢትዮጵያ ...»፣ «ኢትዮጵያ ...» እንዲል ካስገደዱት አንዱ ሁሉ ነገሩ ኢትዮጵያዊ የሆነው ቡናችን ነው። በዓለም ገበያ ላይ ምርጥ (single origin premium coffee beans ይሉታል) በሚል የሚታወቀው ቡናችን ሰሞኑን ከርዕሰ ዜና፣ ርዕሰ አንቀፅ ... ጀምሮ የሚዲያዎቹን ሙሉ ቀልብ ተቆጣጥሯል። እኛ አስቀድመን የኢኮኖሚ ዋልታችን ቡና መሆኑን አምነን እንደዘመርነው፤ እነሱም በራሳቸው መንገድ ንጉሥነቱን አምነው በመዘመር ላይ ናቸው።

እያልን ያለነው፣ «የኢትዮጵያ ቡና» (ኢትዮጵያን ኮፊ) ነገር የፊት ገፅ ቦታን እንደያዘ እዛው ሲሆን፤ እስካሁን ወደ ውስጥ ገፆች ስለመግባቱ ምንም ፍንጭ የለም። ጉዳዩ እንዲህ ነው፤ሰሞኑን የብራዚል ቡና በውርጭ በመመታቱ ምክንያት ከጥቅም ውጪ ሆነ። በመሆኑም የዓለም ገበያ በቡና ድርቅ ተመታ። ለዚህ ድርቅ መፍትሄ ሆኖ የተገኘው ደግሞ የኢትዮጵያ ቡና ነው። በመሆኑም፤ በፍፁም ለማመን በሚያስቸግር ደረጃ አንድ ኪሎ የኢትዮጵያ ቡና 881.10 (ዶላር) ላይ ሄዶ ቁብ አለ።

መች ይሄ ብቻ፣ አፍታም ሳይቆይ 884.50 (ዶላር) ከኢትዮጵያ ቡና አድናቂዎችና ሱሰኞች (አሜሪካ ከሁሉም በላይ ተጠቃሚ ነች)፣ ጀርመን፣ ቤልጂየም፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ጃፓን፣ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ጣሊያን፣ ፈረንሳይ፣ እና አውስትራሊያ - እነዚህ በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ቡና ተጠቃሚዎች ናቸው) እጅ እየተቀበለ ነው። በዚህ ምክንያት የሰሞኑ የዓለም ሕዝብ የጋራ መዝሙር «የኢትዮጵያ ቡና ...» ሆኗል። ይህ እንግዲህ አንዱና ያለንበት የእርስ በርስ ጦርነት እንዳናየው የጋረደን እውነታ ነው።

ሌላው የስንዴ ምርታችንን የተመለከተው ጉዳይ ነው፤ ዜናውም "Despite an ongoing civil war and a record drought, Ethiopia's wheat production is expected to jump 70% this year as it seeks to reduce reliance on food imports." ይለናል – በዚህ ሁሉ የእርስ በርስ ጦርነት መሀል በዘንድሮው አመት የስንዴ ምርታችን ተስፈንጥሮ ከ70 በመቶ በላይ እድገትን እንደሚያመጣ ሲነግረን። ዜናው ይህ የስንዴ ምርት ኢትዮጵያን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከተረጂነት እንደሚያላቅቃትም ያትታል።

www.icarda.org ድረ-ገጽ ዜናም " The TAAT [Technologies for African Agricultural Transformation] project sets the country firmly on the path to achieving wheat production self-sufficiency by 2025" በማለት በ2025 ኢትዮጵያ ስንዴ ተረጂነትን ቻው እንደምትል ብቻ ሳይሆን ለሌላውም እንደምትተርፍ ከወዲሁ ተናግሯል። ሌላስ?

ሌላው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛው የውሃ ሙሌት መጠናቀቅና ኃይል ማምረት መጀመሩ ነው፤ ይህም የኢትዮጵያን የወደፊት ተጠቃሚነት፤ እንዲሁም፣ የአፍሪካ የኃይል ምንጭ በመሆን አህጉሩን እንደምታስተሳስር እየተሰራጨ ያለው ዜና ዘገባ ነው።

ሁሉም በሚባል ደረጃ ህዳሴውን በተመለከተ እያስተጋቡ ያሉት ድምፅ ተመሳሳይ ነው፤ እሱም የኢትዮጵያ ግድቡን የመገንባት ውሳኔ ትክክል መሆኑንና የወደፊት ተጠቃሚነቷን ከወዲሁ የሚያረጋግጥ ነው የሚል ነው።

ሌላው የውጭ ባንኮችን ወደ አገር ቤት ገብተው እንዲሠሩ የመፍቀዱ ጉዳይ ነው፤ ይህ በሁለት መልኩ እየታየ የሚገኝ ይሁን እንጂ አብዛኛው የአስተያየት ሰጪዎች አስተያየት የመንግሥት ውሳኔ (መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ እንዳለ ሆኖ) ትክክለኛ መሆኑ ላይ ያሰመረ ነው።

ሌላው በቴሌኮሚዩኒኬሽኑ ዘርፍ ያለው ሁኔታ ሲሆን፤ የሳፋሪና ህዋዌ ኩባንያዎች፤ እንዲሁም ኢትዮጵያ ይካሄዳል ተብሎ እየተጠበቀ ያለው ዓለም አቀፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጉባኤ የኢትዮጵያ ጉዳይ የበርካታ ዓለም አቀፍ (በተለይም የቢዝነስ) ሚዲያዎች ሰሞንኛ ርዕሰ ጉዳይ በመሆን እየሄደ ያለ «ስቶሪ» ነው።

በውጭ ግንኙነት በኩልም እንዲሁ የስኬት ዜናዎች በብዛት እየሄዱ ያሉበት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤ አንዱና ብዙዎችን ያነጋገረው የኢትዮ-ፈረንሳይ ግንኙነትና የፈረንሳይ የሀይድሮ ኃይል መቆጣጠሪያ ተቋም (ደብረ ዘይት አካባቢ) መገንባት የሚያስችል የ10 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ማድረጓ ነው።

ፈረንሳይ እስከ ዛሬ ከአፍሪካ ጋር የነበራትን ግንኙነት በማደስ፤ ሙሉ ለሙሉም ወደ «አብሮ በመሥራት አብሮ ማደግ» መለወጧ ነው። ሩሲያ ለኢትዮጵያ 162 ሚሊዮን ዶላር ብድር መሰረዟም እዚሁ ጋ ሊጠቀስ የሚችል ነው።

ሌሎችም በርካታ ዓለምንም እያነጋገሩ ያሉ ስኬቶች አሉ። ባለንበት የጨለማው ዘመን ተግባርና ወቅታዊ ሁኔታ የራሳችንን ስኬቶች ራሳችን እንኳን መገንዘብ አልቻልንም። 2015 ዓ.ም ከዚህ ያወጣናል የሚል የብዙዎች እምነት አለና ኃላፊነትን ከመወጣት ጋር «ወደ ላይ ...» በሚለው መሠረት ለዛሬ እዚህ ላይ እናቆማለን።

## ነፃ ሃሳብ

# ከሰብአዊ እርዳታው በስተጀርባ ያለው ሴራ

**ዘካርያስ ዶቢ**

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1985 / በእኛ አቆጣጠር 1977 ዓም አካባቢ ይመስለኛል/ ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተ ከፍተኛ ድርቅ አያሌ ኢትዮጵያውያን ለረሃብ አደጋ ተጋልጠው ነበር፡፡ ህብረተሰቡን ድርቁ ሊያስከትል ከሚችለው ረሃብና የመሳሰሉት አደጋዎች ለመታደግ ታዲያ አንድ ግዙፍ የተባለ አለም አቀፍ የእርዳታ ማሰባሰብ ኮንሰርት በተዋቂው አይርላንዳዊ አርቲስት ሰር ቦብ ጌልዶፍ አስተባባሪነት ተካሄደ፡፡ በአዚህም ዝግጅት በርካታ የአለም ሀገሮችና ቁጥር ስፍር የሌላቸው/ ካውንትለስ ይላቸዋል መረጃው/ ለጋሾች እንደተሳተፉበትም ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡ በእርዳታ ማሰባሰቡም 100 ሚሊየን ዩሮ ወይም 136 ቢሊየን ዶላር ተገኝቷል፡፡

በፈረንጆቹ ሜይ 11 ቀን 2010 በወጣ የጀርመኑ መገናኛ ብዙሃን ጀቼወሌ ዘገባ ላይ እንደተጠቆመው፤ አሸበሪው ትህነግ ይህን ገንዘብ በወቅቱ የትግራይ እርዳታ ድርጅት በሚል ይጠራ ለነበረውና የቡድኑ አንድ ክንፍ ለሆነው ማረት ለተባለ ድርጅት ባልተገባ መንገድ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፤ ቡድኑ ከዚህ ገንዘብ የተወሰነውን ለጦር መሳሪያ መግዣ እንዳወለውም በስደት በውጭ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ የቀድሞ የትህነግ አባላት አጋልጠዋል፡፡ በእርዳታ የተለገሰው ስንዴ እንዴት ተደርጎ እንደተሸጠ ጭምር እነዚህ የፓርቲው የቀድሞ አባላት ማጋለጣቸውን መረጃው ይጠቁማል፡፡

ይህን መረጃም አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በስፋት ተቀባብለውታል፤ ሲአይኤ ጭምር ህወሓት የምእራባውያኑን የእርዳታ ገንዘብ ላልተገባ ተግባር አውሎታል በሚል ሪፓርት አቅርቦበትም አንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

አሸበሪው ትህነግ በወቅቱ ከደርግ ጋር ይዋጋ ነበርና እርዳታውን ለተራበው የትግራይ ህዝብ በቀጥታ ከማድረስ ይልቅ ያደረገው የተወሰነውን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ መግዣ አዋለው፤ ትልቅ ቅሌት፡፡ አሁንም ማስ ማስ ፣ ገለጥ ገለጥ ላደረገ የቡድኑ ቅሌት ከዚያም ቀደም ብሎ ሊጀመር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፤ የቡድኑ ነውር በረሃብ ለተጠቁ ኢትዮጵያውያን አለም የለገሰውን እርዳታ ለጦር መሳሪያ መግዣ ካወለበት ከዚህ አሳፋሪ ተግባሩ እንደሚጀምር ይዘን ስለማንነቱ መግለጽ ይቻላል፡፡

እወክልሃለሁ ያሉትን ህዝብ ህይወት ለረሃብ አጋልጦ በእርዳታ በተሰበሰበ ገንዘብ ሌላ የሞት ድግስ ለማውጣት የጦር መሳሪያ ከመግዛት በላይ ወንጀል የለም፡፡ የስንቱን የትግራይ ህዝብ ህይወት ከሞት አፋፍ ሊመልስ የሚችል እርዳታ ነው ሀገርን ለመውጊያ የሚውል መሳሪያ መግዣ የዋለው፡፡

የመንግስት ምንአልባትም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ የሰብአዊ እርዳታና በእዚህ ላይ ያለ አመለካከት ትርጉም ጤነኛ ነው፡፡ ቃሉ እንደሚገልጸው ማለት ነው፡፡ የአሸባሪው በድን የሰብአዊ እርዳታና በእዚህ ላይ ያለው አመለካከት ትርጉም ግን ከዚህም ይዘላል፡፡

አሸበሪው ትህነግ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ከዘራቸው አሜኬላዎች አንዱ ‹‹እርዳታ›› እና እሱ ላይ የተመሰረተው አመለካከት ነው፡፡ ይህ የጦርነት አባዜ የተጠናነው ቡድን ጦርነቱን ሁሉ ከእርዳታ ጋር ያስተሳሰረ ነው፡፡ የጦርነቱ ሀብት የሚገኘው በሰብአዊ እርዳታ ስም ከሚሰበሰበው ገንዘብና አጋሮች ጋር ይያያዛል፡፡

ቡድኑ ከእያንዳንዱ እርዳታ ጀርባ የራሱ ስውር ተልእኮ አለው፡፡ ከእያንዳንዱ የእርዳታ እንቅስቃሴ ብዙ የሚዘርፈው ያለው በመሆኑ ረሃብ መስራትን፣ ጦርነት መስራትን/ ራሱም ጦርነት መስራት እንችላለን ይላል/ እርዳታ ማሰባሰብን እንደ ህልውናው መሰረት አድርጎ ይቆጥራል፡፡ ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውጪ ህልውና አለኝ ብሎ አይመለከትም፡፡

እርዳታ ለመሰብሰብ ምክንያት አያጣም፡፡ የረሃብ ስጋት በሌለበት የረሃብ ስጋት ይሰራል፡፡ ግጭት በሌለበት ግጭት ይፈበርካል፤ ጦርነት በሌለበት ጦርነት ይሰራል፡፡ እነዚህ አደጋዎች ደግሞ ንጹኃን ይገድላሉ፤ ያፈነቅላሉ፡፡ ለእዚህ ደግሞ እርዳታ ይጠየቅበታል፡፡ ሌላ የእርዳታ ማሳ ተዘጋጀ ማለት ነው፡፡

> **አ**ሸባሪው ትህነግ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ከዘራቸው አሜኬላዎች አንዱ ‹‹እርዳታ›› እና እሱ ላይ የተመሰረተው አመለካከት ነው። ይህ የጦርነት አባዜ የተጠናነው ቡድን ጦርነቱን ሁሉ ከእርዳታ ጋር ያስተሳሰረ ነው፡፡ የጦርነቱ ሀብት የሚገኘው በሰብአዊ እርዳታ ስም ከሚሰበሰበው ገንዘብና አጋሮች ጋር ይያያዛል፡፡

እርዳታ እሱ በትግራይ የዘራው አሜኬላ ነው ፤ አሁንም መዝራቱን ቀጥሎበታል፡፡ በኢትዮጵያ አድራጊ ፈጣሪ በነበረበት የ27 አመት የስልጣን ዘመኑም ወደ ሁለት ሚሊየን የሚጠጋ የትግራይ ህዝብ በሴፍቲኔት መርሀ ግብር በኩል ተረጂ ነበር፡፡ ልብ በሉ እንግዲህ ቡድኑ በልማት ድርጅቱ በኩል አያሌ ኢንዱስትሪዎችንና የንግድ ተቋማትን እያንቀሳቀሰም፣ የሀገሪቱን ሀብት ሙጥጥ አርጎ ወደ ውጭ እያጋዘም፤ በአጠቃላይ ባለጸጋም ሆኖ ነው እንግዲህ ህዝቡ እርዳታ ጠባቂ ሆኖ እንዲቆይ ያደረገው፡፡ ይህ የሆነው በምክንያት ነው፡፡ ከእርዳታና ከእርዳታ በስተጀርባ የሚያገኘው ጥቅም እንዲቀጥል ብቻ አይደለም አንዲጠናከር ጽኑ ፍላጎት ስላለው ነው፡፡

በሚከፍታቸው ጦርነቶች ሁሉ የትግራይን ህዝብ እንደ ሰብአዊ ጋሻ ይጠቀማል፤ ለጦርነቱ ይማግዳቸዋል፤ አንዱን አስልጥኖ አንዱን ደግሞ መናጆ አርጎ ወደ ጦር ግንባር ይልካቸዋል፡፡በእዚህ ሳቢያ አርሶ አደሩ እና ልጆቹን የግብርና ስራቸውን ማከናወን አይችሉም፤ ህዝቡን እርዳታ እየለመነ ማኖሩን መደበኛ ስራ አርጎታል፡፡

ሰሞኑን ባነበብኩት መረጃ ደግሞ እጃቸውን ለጥምር ሀይሉ የሰጡ የቡድኑ ምርኮኞች እርዳታ አይተው እንደማያውቁ ጠቁመዋል፤ አገኘን ያሉትም ከወራት በፊት ያገኙ ናቸው፡፡ እርዳታው በከባድ መኪና ተግተልትሎ ወደ ክልሉ ሲገባ የተመለከተ የዋሀ እንግዲያው ወዴት ገባ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ እርዳታ ቢትረፈረፍም ቡድኑ ሁሌም ስለረሀብ እንዲወራ ስለሚፈልግ፣ የእርዳታ አጀንዳ ጨርሶ ከቡድኑ አይወርድም፡፡

መንግስት በትግራይ ክልል በተካሄደው የህግ ማስከበር ዘመቻ ወቅት አርሶ አደሩ የመኸር እርሻውን በሚገባ እንዲያከናውን የትግራይ ህዝብም ራሱን ቆም ብሎ እንዲመለከት በሚል መከላከያን ከትግራይ ሲያስወጣ የሆነውም ይሄው ነው፡፡

ያ ወቅት ለመኸር ወቅት እርሻ ዝግጅት የሚካሄድበት ነበር፡፡ የክልሉ ግብርና ቢሮ ለግብርና ስራው ተገቢው ማደበሪያና ምርጥ ዘር በወቅቱ ካልቀረበ ቀጣዮቹ አመታት ለትግራይ ህዝብ አስከፊ ይሆናሉ ማለቱን ተከትሎ መንግስት በክልሉ ከተጠየቀው በላይ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦ ነበር፡፡ ቡድኑ ለትግራይ ህዝብ የሚቆረቆርና፣ በእርዳታ መኖር ትክክለኛው የህይወት መስመር አለመሆኑን ቢገነዘብ ኖሮ፣ ይህን ግብአት ይዞ አርሶ አደሩ ተግቶ አንዲሰራ ማድረግ ነበረበት፡፡ እሱ ግን አርሶ አደሩንና ልጆቹን በጦርነቱ በማሰለፍ የአማራ እና አፋር ክልሎችን ወረረ፡፡

በመሰረቱ ቡድኑ የትግራይ ክልል አርሶ አደር ምርታማ እንዲሆን አይፈልግም፡፡ አርሶ አደሩ አመረተ ማለት ቡድኑ ለተለያየ አላማ የሚፈልገው እርዳታ ቀረበት ወይም ቀነሰበት ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በእርዳታ ብዙ ለተጠቀመ፣ እርዳታ ሁሉ ነገሩ ለሆነው አሸባሪው ትህነግ ፈጽሞ አይዋጥም፡፡

የትግራይ ህዝብ በዚህ ከይሲ ታግቷል፤ በእርግጥም እርዳታ ያስፈልገዋል፤ አሁንም ነገም ሰብአዊ እርዳታ ይድረስለት፡፡ አሸበሪው ትህነግ ግን ነገሮችን በእዚህ ልክ አይመለከትም፡፡ እርዳታ ጨርሶ አንዲቆም አይፈልግም፡፡ ያ ሁሉ ከባድ መኪና እርዳታ ጭኖ እየተግተለተለ ወደ መቀሌ ሲጓዝ፣ በዚያ ሁሉ የአውሮፕላን በረራ ሰብአዊ እርዳታ ወደ መቀለ ሲጓጓዝ ከሰፊው እርሻው አዝመራ እንደሰበሰበ አርጎ ሳይቆጥር አይቀርም፡፡

ከእያንዳንዱ እርዳታ ጀርባ ትልቅ የጥፋት ፕሮጀክት አለው፡፡ ልጆቹን ለጦርነት ያላሰለፈ የትግራይ ቤተሰብ እርዳታ አይሰጠውም፤ ለህብረተሰቡ መድረስ ያለበት እርዳታ የቡድኑ ታጣቂዎች ምሽግ እንዲሁም ምርኮኞቹ እጅ ተገኝቷል፤ የተማረኩ አዋጊዎቹ ኪስ ሳይቀር የእርዳታ ብስኩት ተገኝቷል፤ የቡድኑ መሪዎች ጓዳ ጎድጓዳም ቢፈተሽ ይሄው ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ስህተት አይሆንም፡፡ ሰብአዊ እርዳታን ለታጣቂዎች መመልመያ መሳሪያና ለታጣቂና ጀሌዎቹ ስንቅ ያውላል፤ ከዚህም ከሰብአዊ እርዳታ ጀርባ ብዙ የጥፋት ተልእኮዎች ያሉት መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፤ እርዳታ ለማጓጓዝ ወደ ትግራይ የገቡ ከባድ መኪኖች ታጣቂ፣ ስንቅና ትጥቅ ወደ ጦር ሜዳ ያጓጉዛሉ፤ ይሄ አምና ሆኗል፤ እርዳታ ይዘው መቀሌ ከገቡ ከባድ መኪኖች በርካታ የሚሆኑት ዘንድሮም አልተመለሱም ሲባል ዘንድሮም እንደ አምናው ተደርጓል ማለት ነው፡፡ በዚህ ላይ ዘንድሮ ደግሞ ለሰብአዊ አገልግሎት የተከማቸን የአለም ምግብ ፕሮግራም ነዳጅ ዘረፏል፡፡

እርዳታ በእዚህ መልኩ የሚጠቀም ቡድን እርዳታ እንዲያበቃ ስንዝር አይደለም የጋት ያህልም አይንቀሳቀስም፤ የእርዳታ አመለካከትም ከውስጡ ሊጠፋ አይችልም፤ ይልቁንም የበለጠ ስትራቴጂያዊ ለሆነ የጥፋት መንገድ እንዲውል ማሴሩን ይቀጥላል እንጂ፡፡

በጤነኛ መንገድ ለሚሰራ አካል ያ ሁሉ እርዳታ እየተግተለተለ በከባድ መኪና ወደ ትግራይ ክልል ሲገባ፣ በበርካታ የአውሮፕላን ምልልስ እርዳታ ሲጓጓዝ መመልከትም ሆነ ሁኔታው እንዲቀጥል ምክንያት መሆን ያሳፍራል፡፡ አምናም ዘንድሮም ይሄ ሲሆን በእርግጥም ሊያሳፍር በተገባ ነበር፡፡ ከዚህ አይነቱ ህይወት ለመውጣት ርብርብ ማድረግ እንጂ ይህን ሁኔታ የሚያባብስ ተግባር ውስጥ መዘፈቅ በሽታኛነት ነው፡፡

ቡድኑ በትግራይ በረሃብ ስም ከአለም እየተሰበሰበ ያለው እርዳታ የትግራይን ልጆች እስትንፋስ ለማቆየት ሳይሆን የሚያውለው ሲጥ ለማድረግ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የሰራዊቱ ስንቅ ከየት ይገኛል ተብሎ ሲታሰብ መቼም ከአርሶ አደሩ ማሳ ወይም ከአለም አቀፍ ገበያ ተሸምቶ አይባልም፡፡ በታጣቂዎቹ ምሽግና በየታጣቂው ኪስ እየተገኘ ያለው የእርዳታ ምግብ የሚያስተላልፈው መልእክትም ይህን አይደለም፤ ከእርዳታ ነው፡፡

ይህች ሀገርና ይህ ህዝብ ከፉኛ እየተወጋ ያለው እርዳታን ተገን ባደረገ ቡድን ነው፡፡ የአሸበሪው ትህነግ ጉዳይ የጊዜ ጉዳይ ይሆናል እንጂ በአንድም ይሆን በሌላ መንገድ መፍትሄ ያገኛል፡፡ መንግስት ከዚያ ቀጥሎ ቡድኑ በትግራይ ምድር የተከላቸውን እርዳታና የእርዳታ አመለካከቶች መንቀል ትልቁ ስራው ይሆናል፤ የእርዳታ ጠባቂነት ፋይል መዘጋት ይኖርበታል፡፡

# የወራት ሁሉ አውራ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



ኢትዮጵያውያን ጊዜን የማሞገስ፤ለጊዜ የመዝፈን ባህል አላቸው። ክረምትም ሆነ በጋ እንዲሁም ልምላሜም ሆነ ድርቅ በዘፈኖቻችን ውስጥ የተለየ ትርጓሜ ተሰጥቷቸው ይዘፈንላቸዋል። ከሁሉም በላይ መስከረም ደግሞ የተለየ ተደርጎ የሚዘመርበት እንደሆነ መናገር ለቀባሪው አረዱት ነው። ለመሆኑ ይህ ወር የወራት ሁሉ ቁንጮ ተደርጎ ለምን ተወሰደ፤ የተለየ ግጥምና ዘፈኖችስ ለምን ወጡለትና መሰል ነገሮችን ስናነሳ ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ እንችላለን። መጀመሪያ ግን ከተዘፈኑት ዘፈኖች ጥቂት እንበላችሁና ወደዋናው ጉዳይ እንገባለን።

**ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ**
**የእኔ ቆንጆ አጊጣ ተውባ**
**አምሯ ደምቃ በአበቦች ታጅባ**
**ያቻትና መጣች ውብ አበባ ይላል።**
**ሌላም ልጋብዛችሁ። የአመልማል አባተን ዘፈን።**
**የክረምቱ ወር አልፎ ለበጋው ለቋል፣**
**ሜዳው ሸንተረሩ ጋራው በአበቦች ደምቋል፤**
**ሸሞንሟናዬ ውብ ሽቅርቅሩ**
**ድረስ በአውደ አመት በአገር በመንደሩ**
**በወራት መጀመሪያ በአዲስ ዓመት መግቢያ**
**በል ፈጥነህ ድረስልኝ በወዳጅ ዘመድ መሰባሰቢያ። ትላለች።**

ስለመስከረም ያልዘፈነ፣ ያልዘመረ የለምና ሁሉንም ዘርዝረን ስለማንችል በአረጋኸኝ ወራሽ ዘፈኑን እናጠቃል።

**እሰይ አበባው እሸቱ ደርሷል፤**
**ሰፈር መንደሩ አረንጓዴ ለብሷል፤**
**ገደል ሸለቆው ታጥሮ በአበባ፤**
**አደይ አበባ አመስከረም ጠባ፤**
**የሰላም የፍቅር የፍስሃ አዝመራ፤**
**ሸጋ ሸጋ ታብቅል እሰይ ምድር ታፍራ፤**
**የመከራ ዘመን ያዘን ስቃይ ያብቃ፤**
**ሀብት በመስከረም ይኸው ትታይ ደምቃ፤**
**መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ፤**
**ቤት ለእንቦሳ በሏት የልቤን እንቦሳ።**

መስከረምን የዚህ ሁሉ ዘፈን ባለቤት ያደረጋትና የወራት ሁሉ ቀንዲል ያስባላት ምንድነው ከተባለ ምክንያቱ ብዙ ነው። ለአብነት ጥቂቶቹን እናንሳ። የመጀመሪያው ይህ ወር እንደ እኛ ኢትዮጵያዊን የዘመን አዋጅ የሚነገርበት ወር መሆኑ ነው። ዓመታችንን ስንቆጥር አንድ ብለን የምንጀምረው መስከረምን መነሻ አድርገን ነው። የ13 ወር ጸጋ የተባልነውም መስከረም አንድ ብለን ሰላሳ ቀናትን ደፍነን ትርፎቹን ጳጉሜን ብለን ስለሰየምን ነው።

ሌላው የመስከረም ወርን ታላቅ ወር የሚያደርገው ፍካትን፤ ደስታንና አብሮነትን የሚያበስር መሆኑ ነው። ለዚህም ብዙ ሊቃውንትና ጸሐፍት ምስክሮች ናቸው። ከእነዚህ መካከል መዝሙረኛው እና የዜማ ቀማሪው ቅዱስ ያሬድ አንዱ ሲሆን፤ በመፀሐፈ ድጓው ላይ የተለያዩ ሀሳቦችን አስፍሮ እናገኘዋለን። ለአብነት አንዱ ‹‹ኀለፈ ክረምቱ ጸገዩ ጽጌያት!›› ያለው ነው። ይህ ማለት በአማሪኛው ክረምቱ አለፈ አበቦችም ፈኩ የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል።

ታዋቂው ደራሲ በዓሉ ግርማም ‹‹ደራሲው›› በተሰኘው ልቦለዱ ላይ የመስከረምን መጥባትና ገጸ በረከቱን በተመለከተ እንዲህ ሲል አብራርቶታል። ‹‹መስከረም ጠባ። የመስከረም ጮራ ዕንቁጣጣሽ ብላ ተግ አለች። ልጃገረዶች ሳዱላቸው አሳመሩ፤ አደስ ተቀቡ፤ እንሶስላ ሞቁ፤ወንዝ ወረዱ፤ ቄጤማ ለቀሙ፤ ፀዳል ልብሳቸውን ለብሰው፤ አሸንክታባቸውን አጥልቀው ‹ አበባየ ሆይ ለምለም› በማለት ተሰብስበው ብቅ አሉ እንደጮራይቱ።የወርሀ መስከረም ብሩህ ተስፋና ስሜት በምድሪቱ አስተጋባ። ጠፍ እያለ መጣ ምድሩ። ወንዙም እየጠራ። ኩል መሰለ ሰማዩ። ሜዳው፣ ጋራው፣ ሸንተረሩ ወርቃማ የአደይ አበባ ካባ ለበሰ። ደመራ ተደመረ። ተቀጣጠለ ችቦ። ‹ኢዮሃ አበባዬ -መስከረም ጠባዬ› ተባለ።›› በማለት።

ሌላው ሀብተማርያም አሰፋ (ዶ/ር) ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች›› በተሰኘው መጽሐፍ ላይ መስከረም እንዲህ ትገልጻለች። ‹‹ምስከረም›› ከከረመ በኋላ ወይም ክረምት ካለፈ በኋላ ማለት ነው። የመስከረም ወር ዝናብ የሚቆምበት ፀሐይ የምትወጣበት ወንዞች ንጹሕ ውሃ ጽሩይ ማይ የሚጎርፍበት፣ አፍላጋት የሚመነጩበት፣ አዝርዕት አድገው ማሸት የሚጀምሩበት፣ ሜዳዎችና ተራራዎች ሸለቆዎችም በአበባ የሚያሸበርቁበትና የሚያንቆጠቆጡበት ነው።የጨለማ፣ የችግርና የአመጻ ጊዜ የሚያበቃበት ፤ የብርሃን፣ የደስታ የእሸት፣ የፍሬና የጥጋብ ጊዜ የሚጀመርበትና የሚተካበት ነው።

መስከረም ፍቅረኛሞች የሚገናኙበት፤ የተነፋፈቀ ቤተዘመድን የሚቀራረቡበትና የሚደጋገፉበት ፤ ደስታና ፍስሃ የሚበዛበትም ወር እንደሆነ አባባሎቻችን በደንብ ያስረዱናል። ለአብነትም ጥቂቶችን እናንሳ። ‹‹ጉድ ሳይሰሙ መስከረም አይጠባም፤ መስከረም በአበባው ሰርግ በጭብጨባው፤ በመስከረም ስፍራው ሁሉ ለምለም፤ በመስከረም የሚቀድምህ የለም፤ የመስከረም ወፍ ሆንሽ›› የሚሉት ወሩ ምን እንደሚመስል ከሚያሳዩት መካከል የሚነሱ ናቸው።

አሁንም ስንቀጥል ይህ ወር ሌላ ቁንጮ የሚያደርገው ምን መለያ አለው ካልን በስነፈለግና በዘመን አቆጣጠር ብዙ ጥናት ያደረጉት መጋቢ ሀዲስ ዶክተር ሮዳስ ታደሰና መምህር ሄኖክ ያሬድ ፋንታን አዲስ ዓመትን በተመለከተ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባነጋገርናቸው ወቅት ያሉንን ሀሳቦች አብነት በማድረግ እናንሳ።

መጋቢ ሀዲስ ዶክተር ሮዳስ ስናስቀድም መስከረም በኢትዮጵያዊያን በቅብጥ በእስራኤል በቤዛንታይን ባሉ ሀገራት ባሉ ሊቃውንት ትውፊት ሁሉ ዓለም የተፈጠረበት ወር ተብሎ ይወሰዳል ይላሉ። ይህ ወር በጽርዕ “አታኒን”፤ በዕብራይስጥ “ኤታኒም”፤ በእኛ “አታሚን” ይባላል። ፤ ኤታን ማለትም ጥንት፣ መሠረት፣ ጥንተ ወርኅ (የወር መነሻ)፤ ጥንተ ዓመት (የዓመት መነሻ)፤ ጥንተ ዓለም (የዓለም መነሻ)፤ ጥንተ ፍጥረት (የፍጥረት መነሻ) ማለት ነው። የግእዝ ቋንቋ ሊቅ የሆኑት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላታቸው ላይ ኤታኒም በጨረቃ ለሚቆጥሩ ጥቅምት ሲሆን፤ በፀሓይ ቁጥር ለምንጠቀም ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ግን የመስከረም ጫፍ እንደሆነ አስቀምጠዋል።

በመሠረታዊ ነገሩ ቀደምት ግብጻውያን ቱት ብለው የሚጠሩትን የመስከረምን ወር ከክርስቶስ ልደት 3000 ዘመን አስቀድሞ የአዲስ ዓመት መግቢያ የነበረ ሲሆን የዐባይ ወንዝ ጐርፍ ግብጽ የሚያጥለቀልጥበት ጭምር ነበርና የመጥለቅለጥ ወቅት (Season of Akhet (Inundation)) ይሉት ነበር። ይህም ወቅት ከመስከረም እስከ ጥር ድረስ ይቆይ ነበር። በዚህ ወቅት ደማቋ ኮከብን ሳይረስን በልዕልና የሚያዩበትና የኮከቧ በመስከረም 1 መውጣት ለአዲስ ዓመታቸው ምልክት ነበረ።የእነዚህ ሁሉ ጥንታውያን ሀገራት ትውፊት የሚያስረዳን መስከረም ወር የሥነ ፍጥረት መነሻ እንደሆነ ነው።

ሌላው መስከረም ወርን የገለጹበት ደግሞ የመተካከል ወር በማለት ነው። ለዚህ መነሻቸውን የሚያደርጉት ጥንታዊው መጽሐፍ ስንክሳርን ሲሆን፤ “ወርኃ መስከረም ቡሩክ ርእሰ አውራኅ ዓመታት ዘግብጽ ወኢትዮጵያ ሰዓተ መዓልቱ ፲ወ፪ቱ ዕሩይ ምስለ ሌሊቱ ወእምዝ የሐጽጽ” (የተባረከ የመስከረም ወር የግብጽና የኢትዮጵያ ዓመታት ወሮች ራስ ነው፤ የቀኑ ሰዓትም ከሌሊቱ ሰዓት የተስተካከለ ዐሥራ ሁለት ነው፤ ከዚህ በኋላ እያነሰ ይሄዳል) በማለት የመፀው እኩሌታነትን ያነሳበትን ሀሳብ ይጠቅሳሉ። ሀሳቡ በዓመት ውስጥ ቀን እና ሌሊት እኩል የሚሆኑባቸው ጊዜያቶች የሚያሳይ ነውም ይላሉ።

ሌላው መስከረም ለኢትዮጵያውያን ልዩ የተስፋ ምልክት ነው ያሉት ሲሆን፤ ይህንንም በማስረጃ ያብራሩታል። አበው በብኂላቸው “በሰኔ ዝናቡን ወደ እኔ፤ በሐምሌ ልኑር እንዳመሌ” እንደሚሉ በሰኔ ወር የገባው የክረምት ወቅት እየበረታ ሰማዩ በመብረቅ ብልጭታና በነጐድጓድ ድምፅ የሚታጀብበት፤ ከላይ የዝናብ ዶፍ ከሥር ጐርፍ የሚጨምርበት፤ ዐልፎ ተርፎም በረድ የሚዘንብበት የጨለማ፣ የጭጋግ፣ የደመና፣ የጉም ጊዜ ነው።

“በመስከረም ስፍራው ሁሉ ለምለም” እንዲሉ ይህ አስፈሪው የሰኔ፣ የሐምሌ፣ የነሐሴ ወራት ዐልፎ የዐዲስ ዓመት መጀመሪያችን የመስከረም ወር ላይ ግን የበረደውን የምታሞቀው፣ የጨለመውን የምታስለቅቀው፣ የተሰወረውን የምትገልጠው፣ የረጠበውን የምታደርቀው ፀሓይ ከሰወራት ደመና ወጥታ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ብርሃኗን መፈንጠቅ ትጀምራለች። ስለዚህም መስከረም ወር በክረምቱ ዝናብ ረግፈው የነበሩት አበባዎችን በየጋራው በየሸንተረሩ ፈክተው መዐዛን ሲመግቡን፤ ንቦችም አበባዎችን ቀሥመው ጣፋጭ ማራቸውን ለመሥራት ከአበባ ወደ አበባ ሲዘዋወሩ፤ ቢራቢሮዎችም በየመስኩ ሲሽከረከሩ፤ የመስቀል ወፍና የተለያዩ ወፎችም ከተደበቁበት ጐጆዎቻቸው ወጥተው ደስ በሚያሰኝ ዝማሬያቸው ሀገራችንን የሚያደምቁበት ነው ይላሉ።

መምህር ሄኖክ ያሬድ ፋንታ በበኩላቸው፤ ስለ መስከረም ወር ታላቅነት ወይም አውራነት በአማርኛ ግጥም በመጀመር ያስረዳሉ።

‹‹ጨለማው ሲጠፋ ዝናቡ ሲያቆም
ያ የለውጥ ወራት መጣ መስከረም
ሰዎች ይነሣሉ ሊሠሩ ታጥቀው
መስከረም ነውና ብርሃን ሰጪው›› እያለ ዓመቱን ይዘልቃል። ይህ የሆነበት ምክንያትም መስከረም ከባዱ ክረምት ቀዝቀዝ የሚልበት ደመራ ከተለኮሰ በኋላ መሰስ ብሎ የሚወጣበት፣ ምድሪቱ በአደይ አበባ የምታሸበርቅበት ነው። መስከረም ‹‹መስከረም መስከረም የወራቱ ጌታ አበቦች ተመኙ ካንቺ ጋር ጨዋታ›› የተባለለት ወርም ነው።

መስከረም ‹‹መስከረም›› ይባላልም። መዘክረ ዓም (የዓመት መስታወሻ) ተብሎ ዘመን ይሰላበታል፤ በዓላትና አጽዋማት ይታወጅበታል። ይህ ቀን ከዘመነ አክሱም ጀምሮ ክረምቱ ማለፉን አበቦች መፍካታቸውን ለማመልከት ‹‹ተቀፀል ጽጌ›› (አበባን ተቀዳጅ) እየተባለ በየዓመቱ እስከ 15ኛው ምዕት ዓመት ሲከበር ቆይቷል። ከዚያ ወዲህ ግማደ መስቀሉ ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ ግን በመስከረም 10 ቀን እየተከበረ ይገኛል። እንደእርሳቸው አገላለጽ፤ መስከረም በተሞሸረ ዓመት በተቀመረ ቁጥር ሰው መልካም ምኞት የሚለዋወጥበት ወር ነው።

ሰኔ ግም ብሎ፣ የሐምሌን ጨለማ አልፎ፣ የጎርፍ ሙላትን በእኝኝ ተሻግሮና ተንተርሶ በጠንካራው ዝናብ (ውሃ) ምክንያት ብቅ የምትለዋ የአደይ አበባን ይዞ ብቅ የሚል ወርም ነው። ስለዚህም መስከረም ውሃ ያደረገውን ታምር፣ ያስበቀለውን አበባ የምናይበት ወርም ራስ፣ ቁንጮ አውራ እየተባለ እንዲጠራ ሆኗል። ሁሉም አምኖበት እንዲያከብረውና እየተደሰተ እያሳለፈው ይገኛል። አዎ ይህ ሁሉ ምስጢር ያለውን መስከረም ሁላችንም በሐገርኛ ባህላችን እያደመቅነው እንቀጥል በማለት ለዛሬ አበቃን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ማገልገል ከአካባቢ፤ መልማትም ከቀዬ ይጀምራል

ገርማ መንግሥቱ

ማንም ይሁን ማን አካባቢ አለው። የትም ሄደ የት ዞሮ ዞሮ ... ነው ነገሩ። ምንም ዓይነት ሀብት ይትርፍ ይትረፍረፍ ... መጨረሻው «እኸከህ እኸከህ ወደ ዘመድህ ዋጥ» ከመሆን አይዘልም። ይህ እንግዲህ በቅን ልቦና፤ በአገልጋይነት መንፈስ ስንረዳው ነው። እናብራራው።

ይህ ጉዳይ ይብራራ ከተባለ ወሰኑ እስከ ዲያስፖራው ድረስ ይዘልቃል። እንተንትነው ከተባለም ወደ አዳም እና ሄዋን ድረስ ማረጉ አይቀርም። ይሁን እንጂ፣ ከተነሳንበት ርእሰ ጉዳይ፤ አንጻር በአካባቢያቸው ተወልደው፣ እዛው አድገው፣ እዛው ተድረውና ተኩለው እዛው በማገልገል ላይ ያሉትን፤ የዛሬው እንግዳችንን ብቻ ይዘን መዝለቅ ወደናል፡፡

እንዳልነው፣ የዛሬው እንግዳችን ወጣቶች ናቸው፤ ቆይታ ያደረግነውና መረጃ ያገኘነውም በተወካያቸው ወጣት አማካኝነት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ሁሉም በተወካይ ይገለፃል ከሚል ነው።

ወጣት እንዳልካቸው ታምራት ይባላል። ተወልዶ ያደገው በኦሮሚያ ክልል ጎዋ ዎርኮ ቀበሌ ነው። የዛሬው ቀን እንግዳ ያደረግነው እንዳልካቸው (በተፈጥሮው መሆኑ ያስታውቃል) የልጅ አዋቂ፣ ንቁ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ሲበዛም ተግባቢ ነው። ስለ'ሱ የጠየቅናቸው ሁሉ እንደ ነገሩን በሰዎች ተወዳጅ ብቻም ሳይሆን ተመራጭ ነው። ሥራውን ያስኬደዋል ብቻ ሳይሆን ሥራው ራሱ ይሄድለታል። ሰዎችን ላስተባብርና ወደ መልካም ነገር ላምጣ ብሎ ሲነሳም ከሱ ቀድመው የልቡን ነው የሚያደርሱለት። ባጭሩ፣ እንዳልካቸው ታምራት ለሥራ የተፈጠረ የሥራ ሰው ነው። ማህበራዊነት ውስጡ ነው። ተግባቢነት ዕጣ ክፍሉ ነው። ፍጥነት የራሱ ነው። ስኬት አምልጦት አያውቅም። ማገልገል ተፈጥሮው ሲሆን፤ የተቸገሩትን መድረስ እርካታው፤ መመረቅ ትፍህስቱ ነው።

እንዳልካቸው እንዳጫወተን ከሆነ ገና ብዙ የሚቀረው፤ ብዙ እቅድ፤ ከፍ ያለ ተስፋና ራቅ ያለ ራእይ ያለው ወጣት ሲሆን፤ ድርጅታቸውም በዚሁ አቅጣጫ እየሄደ ነው። «አካባቢን፣ ያሳደገን ማህበረሰብ ከማገልገልና ከመመረቅ (ምርቃት ከማግኘት) በላይ ምን አለ» የሚለው እንዳልካቸው በሥራው ዓለም ያጋጠመውን መልካምና ፈታኝ ሁኔታዎች ሁሉ ወደ አጋጣሚ በመቀየር የእድገት መሰላል ማድረግ ላይ ያተኩራል እንጂ ተደናቅፎ አይወድቅም።

ከድርጅታቸው (Abraham and friends Agrochemicals Shop)) ባለድርሻ አካላት አንዱና የበጀትና እቅድ ዘርፉን የሚመራውና «እንዳልካቸው ጎበዝ ነው። ይህ ሁሉ ስኬትና ማህበራዊ አገልግሎት የእሱ ውጤት ነው። ለሌሎች አርአያነቱም እንደዛው» ሲል የእንዳልካቸውን ጥረትና ስኬት የሚናገረው ወጣት አብርሃም ታምራትም ነው፡፡ በስልክ ያነጋገርናቸው የድርጅቱ ተጠቃሚና የጎዋ ወርኮ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ተረፈ ሀብቴ የሚመሰክሩት ይህንኑ ነው።

ስለ ድርጅቱ ጠንሳሽ፣ መስራችና አስተባባሪ እንዳልካቸው ይህንን ያህል ካልን፣ ስለ አጠቃላይ ሥራውና ድርጅቱ ጠይቀነው ያጫወተንን እናካፍል።

**አዲስ ዘመን፡- ሥራ እንዴት ነው?**

**እንዳልካቸው፡-** ሥራ ጥሩ ነው። በጣም ጥሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ድርጅታችሁ መቼ ነው የተቋቋመው፤ ያቋቋማችሁት?**

**እንዳልካቸው፡-** በ2007 ኢ.ም።

**አዲስ ዘመን፡- የድርጅታችሁ መቋቋም ዋና አላማው ምንድን ነው?**

**እንዳልካቸው፡-** ስናቋቁመው ዋና አላማችን የአካባቢያችንን የግብርና ግብአት ተጠቃሚ ኅብረተሰብ፣ በተለይም አርሶ አደሩን ከብዝበዛ መከላከል ነው። ከብዝበዛ መከላከል ሲባል ከከተማ እየመጡ እዚህ ለገበሬው የግብርና ግብአቶችን የሚሸጡ ነበሩ። እነዚህ ነጋዴዎች ዋጋቸው ጤነኛ አልነበረም። የ100 ብሩን 300 እና 400 ብር ነበር ለአርሶ አደሩ የሚሸጡት። ይህ ነገር በጣም ያናድደን ነበር። በመሆኑም «ለምን እኛ ለገበሬው አናቀርብለትም?» የሚል ነገር መጣብን። በቃ፣ ከዚያ ከዚህም ከዛም ብለን፣ ከራሳችንም አድርገንና ተበዳድረን ጀመርነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስትጀምሩ መነሻ ካፒታላችሁ ስንት ብር ነበር?**

**እንዳልካቸው፡-** 47ሺህ ብር።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ምን በማቅረብ ነው ሥራችሁን የጀመራችሁት?**

**እንዳልካቸው፡-** ወሳኝ የሆኑ የግብርና ምርቶችን ለአርሶ አደሩ በማቅረብ ነበር የጀመርነው። ወሳኝ ሲባል እንደ አረም ማጥፊያ፣ የችግኝ ፍሬዎች እና ሌሎችም። በተለይ የዘር ሰዓት ሲደርስ ለዚያ ወቅት የሚያስፈልጉትን ስለምናውቃቸው እነሱን ነበር የምናቀርበው። እራሳችን ግብርና ውስጥ ስላለን ይህንን ማወቅ አይቸግርንም ነበር። ለዚያም ነው «መሸወድ የለብንም፤ አርሶ አደሩም መበላት የለበትም» ብለን የገባንበት።



**አዲስ ዘመን፡- ስመደብራችሁ የሚሆነውን አቅርቦት ከየት ነው ታገኙ የነበረው?**

**እንዳልካቸው፡-** በወቅቱ በማፈላለግ ነበር የምናገኘው። ደብረ ዘይት፣ አዲስ አበባ ... ሰው እየጠየቅን ነበር ገዝተን የምናመጣው። አሁን ያ ችግር ተፈትቷል።

**አዲስ ዘመን፡- በምን መንገድ ተፈታ?**

**እንዳልካቸው፡-** አሁን ሁሉ ነገር እንደ ያኔው አይደለም። ሥራችን በሚመለከተው ሁሉ ታውቆ አስፈላጊው እገዛ እየተደረገልን ነው። የወረዳው (በኦሮሚያ የምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ አድአ ወረዳ) የግብርና ባለሙያዎች የቅርብ ክትትልና እገዛ ያደርጉልናል። ምክርና አስተያየታቸውን ይሰጡናል። ኦዲት ያደርጉናል። የግብርና ግብአቶችን በተገቢው ዋጋ ገዝተን የምናመጣበትን ሁኔታ አመቻችተውልናል። በነጋዴዎች እንዳንበዘበዝ አድርገውናል። ይህ ደግሞ ለእኛ ትልቅ እገዛ ነው። ይህ እገዛ ደግሞ በብዙ መልኩ ከእኛም አልፎ ለአርሶ አደሩ ትልቅ እርዳታና እገዛ ነው። ለአገርም ቢሆን እንደዛው።

ለአርሶ አደሩ በመስክና በኮምፒዩተር የተደገፈ የምክር አገልግሎት እንሰጣለን። በሠርቶ ማሳያ የተደገፈ ነው። እራሳችን ገበሬዎች፣ ከገበሬው የወጣን ስለሆንንና ስለምናውቀው በተግባር ሞክረነው አዋጭ ሆኖ ካላገኘው ለአርሶ አደሩ አንሸጥም። አዋጭ ሆኖ ስናገኘው ብቻ ነው የምንሸጥለትና እንዲጠቀምበት የምናበረታታው። ሁሉ ነገራችን፤ የምንሠራቸው ሥራዎች በሙሉ ዋስትና አላቸው። ይህ ደግሞ ውጤታማ አድርጎን፣ ተአማኒነትን ፈጥሮልን አይተነዋል። አርሶ አደሩም ተጠቃሚ ሲሆን ተመልክተናል። ቤት ለቤት፣ ማለትም በግል በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ከአርሶ አደሩ ጋር ስለምንነጋገር ችግሮችን በቀላሉ ነው የምንፈታው።

ልጆቹ ስለሆንን በማህላችን ምንም ዓይነት የተግባቦትም ሆነ መተማመን ችግር የለም። ይህ እራሱ አንዱ ማሳያ ነው። ከቸገረው ሲያገኝ የሚከፍለው የዱቤ አገልግሎት እንሰጣለን። ብዙውን ጊዜ በስልክ ሁሉ ነው የምንጨርሰው፤ «የት ጋ ነህ፣ የት ልምጣ፣ የት እንገናኝ፣ ይሄ ... አለህ ወይ፣ ዋጋው ስንት ነው ...?» እና የመሳሰሉትን የምንጨርሰው በአብዛኛው በስልክና በማህበራዊ ሕይወት መስተጋብር ውስጥ ነው። ለቅሶም ሆነ ሌላ ቦታ ስንገናኝ ስለ ጉዳዩ እናወራለን። ደብረ ዘይት ወይም አዲስ አበባ ሄዶ የሚያጠፋውን ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብ ... እንዲቆጥብ ዕድሉን እዚሁ ፈጥረንለታል፤ አሠራራችን ሁሉ በሙሉ ዋስትና ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ራሱ ለእኛ አንዱ ደስታና እርካታችን ሲሆን፤ እያገለገልን ነው ብለንም እናስባለን። አዝመራ በሚሰበሰብበት ጊዜም የምንሠራቸው ወሳኝ ሥራዎች አሉ። የውቂያ ማሽኖች ስላሉን በየአርሶ አደሩ ደጅ እየሄድን ውቂያ እንወቃለን። በተለይ ጤፍ እና ስንዴ እኛ ነን የምንወቃው። በዚህም ምን ያህል የአርሶ አደሩን ድካም እንደቀነስን አይተነዋል። ሁለት ቀን የሚፈጅበትን ነው እኛ በሰዓታት ሠርተን የምንጨርስለት። በዚህ ደግሞ አርሶ አደሩ ምን ያህል ደስተኛ እንደሆነ ሁሌም ነው የሚነግረን።

ሌላም አለ። እንደሚታወቀው ይህ አካባቢ ከክረምቱ በተጨማሪ አመቱን ሙሉ የመስኖ ሥራ አለ። አገሩ የተባረከ አገር ስለሆነ ሁሌም እርጥብና ምርታማ ነው። ሁሉም ዓይነት ምርቶች አሉ። አትክልት በየዓይነቱ ነው። ወደ ማዶ፣ ጎዋ ወርኮ ቀበሌ እንኳን ብትሄድ የአትክልት ዓይነቶችን በሙሉ ታገኛለህ። ስፍራው ለምለም ነው ብቻ ሳይሆን ገነት ነው ማለት ይቻላል። እዚህ ጎዲኖም እንደዛው። አልተሠራበትም እንጂ ቢሠራበት የትና የት ባስገኘ ነበር። ልልህ የፈለኩት፣ በዚያው ልክ የእኛም ሥራ አለ። ልክ ለክረምቱ እንደምንሠራው ሁሉ ለመስኖውም እናቀርባለን።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን በማድረጋችሁ ምን ያገኛችሁት ነገር አለ፤ ማለትም የተጠቃሚው ኅብረተሰብ ምላሽ ምን ይመስላል?**

**እንዳልካቸው፡-** በእኛ በኩል የሕዝቡ ምላሽ ያው እንደ ነገርኩ ነው፤ በጣም ደስተኛ ነው። ሁል ጊዜ ምርቃት ነው። ሁል ጊዜ ምስጋና ነው። እኛ ከሁሉም የሚያስደስተን ደግሞ ምርቃቱ ነው። እንደ ምርቃቱ የሚያስደስተን ምንም የለም። ሕዝቡ ሲመርቅህ ከልቡ ነው። የእውነቱን ነው። ለችግሬ ደረስክልኝ ብሎ ሲመርቅህ አንተም ደስ ይልሃል። ካለው ከፍሎ፤ ከሌለው ቀስ ብሎ የሚከፍለውን ግብአት ስለሚወስድ ልክ እንደ ራሱ ቤት ነው የሚቆጥረው። ደግሞም ነው። ካስፈለገም፣ እንደ ሰውየው የገቢ ሁኔታ አይተን ከመጣበት ቀንሰን ሁሉ እንሸጥለታለን።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ አገልግሎታችሁ ከሌላ አካላት ያገኛችሁት ድጋፍ ወይም ማበረታቻ አለ?**

**እንዳልካቸው፡-** አዎ፣ አለ። በመጀመሪያ ድጋፍም ሆነ እገዛ ያገኘነው፣ ቅድም እንዳልኩህ ከወረዳው የግብርና ባለሙያዎች ነው። ከምክር አገልግሎት ጀምሮ ስልጠና ድረስ የዘለቀ አገልግሎትን አግኝተናል። ከዚያም በላይ ደግሞ ባሳየነው ጥረት፣ በምንሰጠው አገልግሎትና ባስመዘገብነው ከፍተኛ ውጤት አዳማ (ናዝሬት) ላይ ተጋብዘን ከፍተኛውን የሜዳልያ ሽልማት አግኝተናል። እገዛው በብዙ መልኩ ነው። እዚህ የደረስነው በእነሱ ድጋፍ ስለሆነ ይህ እንደሚቀጥልም እርግጠኞች ነን።

አሜሪካዊው የልማት ድርጅት (“ዩኤስኤይድ” የሚባለው) እየቀጠለ የሚሄድ የመጀመሪያ ዙር ድጋፍና እርዳታ አድርጎልናል። ለምሳሌ፣ ይህ የምታየው በአብዛኛው በእነሱ ድጋፍ የተገኘ ነው። እዚህ ድረስ በመምጣት ማቀዝቀዣ፣ ባለ መስታወት መደርደሪያ፣ የግድግዳ ቀለም፣ ኮርኒስ፣ ትልቅ ማከማቻ፣ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ ሶላር፣ ቁም ሳጥን፣ ላፕቶፕ፣ መደርደሪያ ....፤ እንዲሁም ከመደብሩ ውጪ ያለውን በራፍ በአስፋልት ማሳመርና ሌሎች ድጋፎችን ሁሉ አድርገውልናል። ይህ ለእኛ ትልቅ ማበረታቻ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ ካፒታላችሁ እንምጣ። ቅድም በ47ሺህ ብር መነሳታችሁን ነግረኸኛል። አሁን ስንት ደርሳችኋል?**

**እንዳልካቸው፡-** 3, 000, 000.00 (ሦስት ሚሊዮን ብር)

**አዲስ ዘመን፡- የወደ ፊት እቅዳችሁ ምንድን ነው?**

**እንዳልካቸው፡-** አሁን ያለነው በትንሹ (ማይክሮ) ደረጃ ነው። እቅዳችን ወደ ላይ መሄድ ነው። ከዚህ መውጣትን አቅደን ነው እየሠራን ያለነው። ለዚህም እንዲያግዘን ያቀድን፤ ያቀድነውንም ያሳወቅን ሲሆን፤ የተለያዩ ብድርና ድጋፎች እንዲመቻቹልን ጠይቀናል። ከእነዚህም አንዱ ትራክተር እንዲሰጠን ወረዳውን የጠየቅነው ነው። እስካሁን ምላሽ አላገኘንም። ምላሽ እናገኛለን ብለን ግን እንጠብቃለን። ሌሎች ነገሮችም እንደዚያው ይመቻቹልናል ብለንም እናስባለን። ይህ ከሆነ በየአርሷደሩ መንደር፣ እርሻ ቦታና በሚሠራበት ሁሉ እየሄድን ለመሥራት ነው ያቀድነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደው እዚህ ደረጃ እስክትደርሱ ምንም ያጋጠማችሁ ችግር የለም? ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ ነበር ማለት ይቻላል?**

**እንዳልካቸው፡-** (ሳቅ) አለ እንጂ፤ በጣም አለ። ዋናውና ደስ የሚለውም እሱን አልፎ እዚህ መድረሱ ነው። ያመነን ሰው ሁሉ አልነበረም። «እነዚህ ልጆች ትምህርት የላቸው፤ እንዴት እንደዚህ ሊደፍሩ ቻሉ?» ተብለን ሁሉ ነበር። ይህ ምንም ማለት አይደለም፤ ይጠበቃል። በመንግሥትም በኩል እንደዚያው ነበር። ከብዙ ፈተናና ማረጋገጥ በኋላ ነው ትክክለኛነታችን፤ አገልጋይነታችን ተረጋግጦ ለእውቅናና ድጋፍ የደረስነው። ጥያቄህን መልሼው ከሆነ የነበረው ሁኔታ ይህንን ይመስል ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ከማኅበረሰቡ ሌላስ የምትሰጡት ማህበራዊ አገልግሎት አለ? እንደው፣ ካለ በሚል ነው።**

**እንዳልካቸው፡-** አዎ፤ በሚገባ አለ። ለሥራ ጉጉ የሆኑ፣ የሥራ ፍቅርና ተነሳሽነት፤ ታታሪና ራእይ ያላቸውን ወጣቶች እንቀርባቸዋለን። ቀርበንም እናግዛቸዋለን። ወደ ሥራ እንዲገቡ እናበረታታቸዋለን። የምንችለውን እያደረግንም እናቋቁማቸዋለን። እስካሁንም ሁለት ወጣቶች እራሳቸውን ችለው በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ እየቀጠሉ ከሚሄዱት ተግባሮቻችን አንዱ ነውና የሚቆም አይደለም። ሌላው በቅጥርም የሥራ ዕድል የመፍጠሩ ጉዳይ ሲሆን፤ ይህም እየሰፋ የሚሄድ እንደሚሆን መገመት አይቸግርም።

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ወጣቶች ናችሁ። በራሳችሁ ተነሳሽነትም ወደ ሥራ ገብታችሁ እዚህ ደርሳችኋል። ከዚህ አኳያ ለሌሎች ወጣቶች ምን መልዕክት ታስተላልፋላችሁ?**


**እንዳልካቸው፡-** እርግጥ ነው፤ እኛ በራሳችን ተነሳሽነት እዚህ ደርሰናል። ተነሳሽነቱም የመነጨው ላሳደገን ማኅበረሰብ፣ አርሶ አደሩ ከመቆርቆር ነው። ያ ማለት ደግሞ፣ እኛም የአርሶ አደሩ ልጅና አካል በመሆናችን ለራስ ከመቆርቆርም ጭምር ማለት ነው። ከዚህ ተነስተን እዚህ ደርሰናል። ወደ ፊት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ለመሄድ አስበንና አልመን እየሠራን ነው። እግዚአብሔር ከፈቀደ ሁሉንም እቅዳችንን እናሳካለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ከዚህ አኳያ ለወጣቱ የማስተላልፈው መልዕክት፣ በቃ ወደ ሥራ እንግባ ነው። በአካባቢው የሚሠራ ሥራ ሞልቷል። አካባቢው ለም ነው። አልተነካም። ሌላው ጋ የቸገረው ውሃ ነው። ያ እዚህ ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። በመሆኑም ልንሠራ ይገባል። በአሁኑ ጊዜ መሥራት ነው የሚያስፈልገው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጠኸን ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**እንዳልካቸው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# በማዕድን ክፍለኢኮኖሚው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ

ስምለም ምንግሥቱ



እቅዱ ባህላዊ ወርቅ አምራቾች የወርቅ ማምረቻ ማሽኖችን ለማቅረብ ድጋፍ እንደሚደረግ አመላክቷል

መንግሥት ከ2012 በጀት አመት ጀምሮ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም የአስር አመት መሪ እቅድ ወጥቶ እየተሠራ ይገኛል። የአገር የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስቀጠል፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር እንዲሁም ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ማሻሻያው አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጣቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎች ማዕድንና ነዳጅ ዘርፍ ይጠቀሳሉ። የማዕድን ዘርፍ በውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ አገር የሚገቡ የማዕድን ውጤቶችን፣ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብአቶችን በአገር ውስጥ መተካትና የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአገር ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ ጥቂቶቹ ናቸው። ዘርፉን በዋናነት የሚመራው ማዕድን ሚኒስቴር ይህን መሠረት በማድረግ ዘርፉ ለኢትዮጵያ የመጪዎቹ አመታት የብልጽግና ጉዞ የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት እንዲሁም በ2022 ዓ.ም የማዕድን ሀብት የብልጽግና መሠረት ሆኖ ማየት የሚል ተልዕኮ ይዞ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆነ ሚኒስቴሩ በማዕድን ክፍለኢኮኖሚ የ2015 በጀት አመት የእቅድ ሰነዱ አመልክቷል።

በዘርፉ የተሳኩ ተግባራትን ለማከናወን በ2014 በጀት ዓመት በሪፎርምና በሠራቸው ሥራዎች ተጨባጭና ትልቅ ተስፋ ያላቸው ውጤቶች ማስመዝገቡን ሚኒስቴሩ በሰነዱ አስታውሷል። ያለፈ ስኬቱን መነሻ በማድረግ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘጋጅቷል። ለበጀት አመት እቅዱም የተለያዩ መነሻዎችን መሠረት አድርጓል።

አንዱ መነሻው የ2014 በጀት ዓመት አጠቃላይ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተሰጡ ግብረ- መልሶችን እንደ ግብዓት ተጠቅሟል። እነዚህ መሠረቶች ለአዲሱ በጀት አመት የእቅድ ሥራው የነበሩበትን ክፍተቶች ለመለየትና አስፈላጊዎቹን የማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሰድ በማገዛቸው የተሻለውን አሠራር በእቅዱ በማካተትና ክፍተቶቹን በማረም የዘርፉን ራዕይ አንግቦ ተቋማዊ ተልዕኮ ለመፈፀም ተዘጋጅቷል።

ከሰነዱ መረዳት እንደሚቻለው፤ የዘርፉን የቀጣይ አስር አመታት ዕቅድ መሠረት በማድረግና በአዲስ መልክ ፕሮግራሞችን በመቃኘት በ2015 በጀት ዓመት ለመተግበር በቂ ዝግጅት ተደርጓል። በዚሁ መሠረትም የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በአምስት ፕሮግራሞች ተዘጋጅቷል። ይህም የዘርፉን ተቋማዊ አቅምና ብቃት የማጎልበት፣ የስነ-ምድር መረጃን ለልማትና ለኢንቨስትመንት የማመንጨት፣ የማዕድን ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት፣ የማዕድን፣ ነዳጅ እና የጂኦተርማል ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የማጎልበት እንዲሁም የማዕድን፣ ነዳጅ እና ጂኦተርማል ምርት አቅርቦት ድጋፍ ፕሮግራሞች በሚል ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል። ለየፕሮግራሙ ስኬትም አግባብነት ያላቸውን ውጤት አመላካች ተግባራትን ታሳቢ ጉዳዮችንም አካቶ ቀርቧል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በእጥረት የተለዩ ጉዳዮችን የማሻሻል እቅዶችንም በ2015 በጀት አመት አቅዱ አካትቷል። ከእነዚህም መካከል የማዕድን ልማት የሚካሄድባቸው ቦታዎችን የፀጥታ ስጋት ለመፍታት ከፌዴራልና የክልል የፀጥታ መዋቅሮች ጋር እንዲሁም ከአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በቅርበት የሚሠራውን ሥራ እና የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚውን ውጤታማነት ለማጎልበት እንዲሁም ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ ያሉትን ክፍተቶች ለመቅረፍ ከክልል ከፍተኛ አመራሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር፤ የቁልፍ ውጤት አመልካች ተግባራትን በሚመለከት ያሉ ውስንነቶችን ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመወያየት ዕቅዱን ወቅታዊ ለማድረግ በጋራ መሥራት፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች በመንግሥትና በኩባንያዎች አቅም እንዲገነቡ በትኩረት መሥራት የሚሉት ይገኙበታል።

በበጀት ዓመቱ የክፍለ ኢኮኖሚውን ውጤታማነት ለማጎልበት የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎችም በሰነዱ ተመላክተዋል፤ የወጪ ንግድ ማዕድናትን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፤ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብአቶችን እና የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት በተለይም የድንጋይ ከሰል፣ ማዳበሪያ፣ ብረት እና የግንባታ ማጠናቀቂያ (finishing Materials) ግብአቶች ላይ በልዩ ትኩረት ይሠራል።

ዘመናዊ የማዕድናት ግብይት ሥርዓት መዘርጋት፣ በዘርፉ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለማሳደግ የሥነ-ምድር መረጃ በጥራትና በሽፋን በማበልፀግ የፕሮጀክት አዋጭነትን የሚያሳዩ የማስተዋወቅ ሥራዎች በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ መዳረሻዎች በስፋት በመሥራት ግዙፍ ኩባንያዎች በዘርፉ ማሰማራት የሚሉትም ከትኩረት አቅጣጫዎቹ መካከል ይገኙበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዘርፉ የተሰጡ ነባር የማዕድን ልማት ፕሮጀክቶችን ድጋፍና ክትትል በማጎልበት የፕሮጀክቶችን የውል አስተዳደርና አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት መሥራት፤የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶች የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ያጎለበቱ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የማዕድናት ዕሴት ማበልፀጊያ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋትና ማጠናከር፤ በባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከክልሎች ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራር የመዘርጋት ሥራዎችን መሥራት፣ በክፍለ ኢኮኖሚው የተማረ የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት እንዲኖር መሥራት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ቁልፍ ከሚባሉ ባለድርሻ አካላት ጋርም ቅንጅታዊ ሥራ ለመሥራት ስላስቀመጠው አቅጣጫም ሰነዱ እንዳመለከተው፣ የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚ ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ያለውን አስተዋጽኦ እንዲወጣ፣ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ የማዕድናት ምርትን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ማምረት፣ ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ኢንዱስትሪ ግብአቶችና የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ መተካት እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራ ተልዕኮዎችን ለማሳካት ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የሆኑት ክልሎች፣ ኩባንያዎች፣ የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች እንዲሁም ልዩ ልዩ ተግባርና ኃላፊነት ያላቸው የመንግሥት ተቋማት ናቸው።

ከዚህ አኳያ የክልል ባለድርሻ አካላትን በሚመለከት ከክልል ቢሮዎች፣ የከተማ መስተዳድሮች ጋር በመሆን በጋራ ከዕቅድ ዝግጅት እስከ አፈፃፀም መሥራት፣ የባህላዊ ማዕድናት አምራቾችንና የተለያዩ ባለፈቃድ ኩባንያዎችን በመደገፍ ለሥራ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጠር ማድረግ፣ በዘርፉ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ሕገወጥ የማዕድናት ግብይትን በመቆጣጠር የጎላ አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚገባ ተገልጿል።

ኩባንያዎች በገቡት የውል ስምምነት መሠረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የሚጠበቅ ሲሆን፣የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በየወቅቱ በመከታተል የጋራ መፍትሔ በመስጠት ውጤታማነታቸውን ማጎልበት፤ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናትን በማምረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ የሚገኙትን የባህላዊ ማዕድናት አምራቾችን አሠራራቸውን፣ አመራረታቸውን እንዲሁም አደረጃጀታቸውን ማሻሻል ትልቅ ትኩረት መስጠቱ በሰነዱ ተጠቅሷል።

ይህን የሚያግዝ የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች አደረጃጀት፣ አመራረትና አሠራር ማሻሻያ ፕሮጀክት ተቀርፆ ወደ ትግበራ መግባቱ ተመልክቷል። በመሆኑም ለዚህ የሚያግዙ ማሽነሪዎችን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል፤ በባህላዊ የማዕድን ማውጣት ዙሪያ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም ለፖሊሲ ግብአትነት ጥናትና ምርምር እንዲደረግ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተደረገውን የጥናት ስምምነት አጠናክሮ ማስቀጠል፤ ከትምህርት ሚኒስቴር እና በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ በመሥራት የማዕድን ዘርፍ በቴክኖሎጂና በምርምር እንዲደገፍና ዘርፉ በተማረ የሰው ኃይል እንዲመራ የማዕድን የትምህርት ክፍሎች ተጠናክረው ጥራት ያለው የተማረ የሰው ኃይል በስፋት ማበርከት እንዲችሉ በጋራ መሥራት የሚልም በሰነዱ ተመልክቷል።

ሚኒስቴሩ የማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች ግልጸኝነት የሰፈነበት፤ ዘመናዊነትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው እንዲሆን ተቋማዊ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም አድጎና በልጽጎ ለዘርፉ ዓበይት ተግባራት ውጤታማነት የተሻሻለና ብቃቱ የተረጋገጠለት የመልካም አስተዳደር ችግሮች የቀነሱበት፤ ዘላቂነት ያለው ተቋም ማድረግ ከዋና ዓላማ ተግባራቶቹ መካከል መሆኑን በሰነዱ አብራርቷል።

ሚኒስቴሩ በበጀት አመቱ ያቀዳቸውን ሥራዎች ለመፈጸምም የያዘውን በጀትም ከእቅዱ ጋር አያይዞ በዝርዝር አስቀምጧል። የበጀት አመቱን ዕቅድ ለመፈፀም ለመደበኛ ሥራዎች መተግበሪያ ብር60 (ስልሳ) ሚሊዮን እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 60 (ስልሳ) ሚሊዮን በድምሩ ብር 120.00፣ ሚሊዮን በጀት ተይዟል። በተጠሪ ተቋማት ማለትም ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት መደበኛ ሥራዎች መተግበሪያ ብር 85 ነጥብ 162 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ብር 200 (ሁለት መቶ) ሚሊዮን በድምሩ ብር 285 ነጥብ 162 ሚሊዮን የተያዘ ሲሆን፣ ለማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መደበኛ ሥራዎች መተግበሪያ ብር 81 ነጥብ 04 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ብር 60 ሚሊዮን በድምሩ ብር 141ነጥብ04 ሚሊዮን መያዙ ተጠቁሟል። በአጠቃላይ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማት ለሚከናወኑ መደበኛ ሥራዎች መተግበሪያ ብር 226ነጥብ20 ሚሊዮን እንዲሁም ለካፒታል ሥራዎች ማስፈፀሚያ ብር 320.00 ሚሊዮን በአጠቃላይ ብር 546ነጥብ20 ሚሊዮን በጀት ተደግፏል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መልካም አጋጣሚዎች፣ ስጋቶችና የማስፈጸሚያ ስልቶች ብሎ በሰነዱ ካሰፈራቸው መካከልም የሚከተሉት ይገኙበታል። በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚ በተሰጠው ልዩ ትኩረት መንግሥት ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ዘርፉን ለመደገፍ ቁርጠኝነት አሳይቷል።

ኢትዮጵያ ዕምቅ የማዕድን ሀብት ያላት አገር መሆኗ፤ በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ፍላጎት መጨመር፤ አንዳንድ ማዕድናት በዓለም ላይ ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ እየሆነ መምጣቱ በመልካም አጋጣሚ ይጠቀሳል። በስጋት ካስቀመጣቸው ነጥቦች መካከልም በማዕድን አምራች አካባቢዎችና ኩባንያዎች የሚከሰት የፀጥታ ችግር፤ ሕገ-ወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ መኖር፤ ወደ ምርት ይገባሉ ተብለው የሚጠበቁ ፍቃዶች በሚፈለገው ፍጥነት ወደ ምርት አለመግባታቸው እና የኩባንያዎች የአቅም ውስንነት፤ ከፍተኛ ችግሮች ላለባቸው የማዕድን ውጤት አምራች ኢንዱስትሪዎች በአገር ውስጥ የማይገኙ የግብዓት፣ የአላቂ ዕቃዎች እና ለመለዋወጫዎች የሚሆን የውጭ ምንዛሬ እጥረት የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ግቦችን ሊያሳኩ የሚያስችሉ ብሎም ሊያጋጥሙ ይችላሉ የተባሉትን ስጋቶችን በመቀነስ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም የሚከተሉትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች መተግበር ወደ ውጤታማ አፈጻጸም ሊያመጣ እንደሚችል ሚኒስቴሩ ያመነባቸውንም እንደሚከተለው አስቀምጧል። የፀጥታ ችግር እንዲሁም የሕገወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ በተመለከተ ማዕድን የሚመረትባቸው ቦታዎች ከሚመለከተው ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከመከላከያ እንዲሁም ከክልል የፀጥታ ተቋማት ጋር እየተሠራ ያለውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል፣ እንዲሁም የግብይት ማዕከላት በአቅራቢያቸው እንዲከፈቱ ከሚመለከታቸው ጋር መሥራት፤ ኩባንያዎች በገቡት የውል ግዴታ መሠረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን ማጠናከር፤ አምራች ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙበት ሁኔታዎች ላይ ከሚመለከታቸው ጋር በቅርበት መሥራት የሚሉት በዝርዝር ሰፍረዋል።

2015 በጀት አመት በዘርፉ ፕሮግራሞች፣ ዋና ዋና ውጤት አመልካች ተግባራትና ግቦች እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶች የበለጠ እንዲጎለብቱ ከተጠሪ ተቋማት፣ ከክልሎችና ከከተማ መስተዳድር የዘርፉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የማዕድን ክፍለ-ኢኮኖሚው በአገራዊ ብልፅግና ያለውን ፋይዳ ለማሳደግ መረባረብ እንደሚያስፈልግም ሚኒስቴሩ አመላክቷል።

የማዕድን መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጠበቁ፣ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ፤ ለማዕድን ፍለጋና ልማት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማዕድን ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፣ በማዕድን፣ ፔትሮሊየምና ጂኦተርማል ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ፈቃድ በመስጠት፣ ባለሀብቶቹ በገቡት ውል መሠረት ሥራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን መፈጸማቸውን በመቆጣጠር፣ በባሕላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ በማድረግ፤ የማዕድንና ተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሠልጠኛ ተቋሞችን እንደ አስፈላጊነቱ በማቋቋም ሚኒስቴሩ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ተግባራት እንደሆነ በሰነዱ ተብራርቷል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የአያቴ እልልታ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በመዶሻና በኩርንችት ሚስማር ተከብቤ፣ የሰባት ሰዐቷ ጸሀይ አንጸባርቃብኝ፣ በላብ ቸፈፍ ተጠምቄ፣ መሬቱን በጥፍሮቼ ቆንጥጬ፣ ተረከዜ ላይ ተደላድዬ ቁጢጥ ብያለው..ባለፈው ሁለት ሳምንት ቅናሽ ሆኖ ሳገኘው ጥሩ መስሎኝ የገዛሁትን ሶሉ የለቀቀብኝን የቻይና ጫማ እየጠገንኩ። አይ ቻይና እላለው በልቤ። በስራ አጥ ወገቤ አጠራቅሜ የገዛሁት ብልጭልጭ ጫማዬ በሳምንቱ አይሆኑ ሆኖ ሳገኘው። እንደ እኔ በዚች ምድር ላይ ቻይናን የረገመ ሰው ያለ አይመስለኝም። ቻይና እንዴት ሰለጠነች ብሎ ለጠየቀኝ የምመልሰው አንድ መልስ አለኝ በብልጠትና በወርቅ ቀለም የተሸለመ አመዳይ እየሸጠች የከበረች የሚል። እንዲህ እንደ እኔ በወርቃማ አሸንጉሊት ተታሎ ብኩን የሆነ ብቻ ነው ቻይናን የሚያውቃት። ብዙ ቀን እንዲህ እንደ አሁኑ ለምስራቅ ደፍ ግንባሬን ሰጥቼ፣ ተረከዜ ላይ ቁጢጥ ብዬ ስፍገመገም አያቴ ምን እየሰራህ ነው ብላኝ ታውቃለች። ምን እየሰራህ ነው ስትለኝ.. ሳምንት የገዛሁት ጫማዬ ሶሉ ወልቆ እሱን እየጠገንኩ ነው ብላት የምትሆነው መሆን ስለሚያስፈራኝ እዋሻት ነበር።

ቻይና ጋፍ ጫማ ብቻ አይደለም የሸጠችልኝ ውሸትንም ነው አብራ የሸጠችልኝ። አያቴን ዋሽቻት የማላውቀው ልጅ ከዛ ጫማ በኋላ ውሸት ጀመርኩ። የቻይና ግፍ መች ይሆን በድሀ ሀገራት ላይ የሚያበቃው? ብዬ ሳልጨርስ የአያቴን እልልታ ከሳሎን ሰማሁት። አያቴ በሆነ ባልሆነው እልል እንዳለች ነው። ዛሬ ከነጋ እንኳን ሰባት ጊዜ እልል ስትል ሰምቻታለው። ልብሳችንን እየበላች መከራ ያሳየችን የቤታችን አይጥ በወጥመድ መያዟን ስታይ እልል ብላ ነበር። የዛሬ ወር የቤታችንን ቄብ ዶሮ የዛሬ ሳምንት ደግሞ የቤታችንን መጫት ዶሮ ከነአራስ ልጆቿ የሰለቀጠው የጎረቤታችን የጋሽ ታፈሰ ጉልቤ ድመት በመርዝ መሞቱን ስነግራት እልል ብላ

**ቻይና ጋፍ ጫማ ብቻ አይደለም የሸጠችልኝ ውሸትንም ነው አብራ የሸጠችልኝ። አያቴን ዋሽቻት የማላውቀው ልጅ ከዛ ጫማ በኋላ ውሸት ጀመርኩ**

ነበር። ማዶ ተሻግራ ያለችው የታላቅ እህቷ ነፍሰ ጡር ላም በሰላም መገላገሏን ስትሰማ እልል ብላ ነበር። የቤታችንን ጣሪያ እየዞረ ከጋሽ ታፈሰ ድመት የተረፉትን ጫጩቶች የሚቀላውጠው ጭልፊት ባልታወቀ ምክንያት መሰዋቱን ስትሰማ እልል ብላ ነበር። አሁን ደግሞ በምን እንደሆነ እንጃ እልል ስትል ሰማኋት። አያቴ መደሰቻ አታጣም። አፏ ለእልልታም ሆነ ለእርግማን ቅርብ ነው። እኛ ቤት ውስጥ በእማዬ እልልታ ሁሌም ሰርግ ሁሌም መልስ አለ።

ወዲያው ጉርምርምታዋን ሰማሁት..በጉርምርምታዋ ውስጥ ስሜ ይሰማኛል። አሽሙርና ለበጣ የቀላቀለ ጉርምርምታ። አያቴ ብዙ አይነት ሴት ናት። እልል ባለች አፏ እርግማን ይቀናታል። አሜን ባለች አንደበቷ ሀሜት ምሷ ነው። ትላንትን እያስታወሰች፣ አምናን እየመለሰች መራገም፣ መነጫነጭ ልማዷ ነው። አልቀየማትም.. ወንድነቴ እንደፈለገች መሆኛዋ ነው። ራሴን ለሀሳቧ፣ ለምኞቷ፣ ለእርግማንና እልልታዋ አሳልፌ የሰጠሁ ሰው ነኝ።

ማረፊያዋ ነኝ..የነጻነቷ ወደብ። እንደ እኔ እንደፈለገች የምትሆንበት ምንም የላትም። እኔም እንደፈለገች ስለምትሆንብኝ ደስ ይለኛል። በአፌ በብልጭልጭ ቀለም ጎድ የሰራችኝን ቻይናን እየረገምኩ በጆሮዬ ደግሞ ስሜን የቀላቀለ የአያቴን እልልታ እያደመጥኩ በሁለት አለም ውስጥ እዋልላለው። ለብዙ ሰዐት ተረከዜ ላይ ቁጢጥ ማለቴ ህመም ስለፈጠረብኝ መቁነጥነጥ ጀመርኩ። መቁነጥነጥ ብቻ አይደለም ሚዛን እየሳትኩ ወዲያ ወዲህ መዋዠቅ ጀመርኩ። ብዙ ሳልቆይ ቂጤ ላይ በሳሳው ሱሪያ መሬት ላይ ተዘረፈጥኩ። መሬት ቻለችኝ። እንደ መሬት ቻይ ምን አለ? መሬት እኔን መቻሏ ገረመኝ። ያን ሁሉ ድካሜን፣ ያን ሁሉ አበሳዬን መቻሏ መሬት ምን ያክል ቻይ እንደሆነች ደረስኩበት። እኛ የሰው ልጆች እኮ በሀጢያታችን፣ በበደላችን፣ በክፋታችን ማንም የማይችለን ነበረን..መሬት ግን ቻለችን።

አያቴ ከእልልታዋ ጋብ ስትል በትሯን ተመርኩዛ ወዳለሁበት ደጅ ወጣች። ድምጽዋን ሰውራ፣ ኮቴዋን አጥፍታ ድንገት አጠገቤ ሳያት ድንግጥ ነበር ያልኩት። ከድንጋጤዬ የተነሳ ጫማዬ ላይ ባለምኩት መዶሻ እጄን ልቀጠቅጠው ምንም አልቀረኝ ነበር። ቶሎ አላየኋትም። ሁሉ ነገሬ ጫማዬ ላይ ስለነበር ከዛ እስከዚህ እስክትደርስ ኮቴዋ ለጆሮዬ ባዕድ ነበር። በሰባት ሰዐቷ ጀምበር የተሳለ በእርጅና ያጎነበሰ ጥላዋ ሲያርፍብኝ ነበር ቀና ያልኩት።

ለጎኔ በቀረበ..ትከሻዬን በሚተሻሽ አቀማመጥ አጠገቤ መጥታ ተቀመጠች። እንደፈለገች ልትሆንብኝ እየተዘጋጀች መሰለኝ። አይኖቿ እንደፈለጉ ሊሆኑብኝ በትዝብት ሲያስተውሉኝ ቀና ባልኩበት አንድ ጊዜ አስተዋልኳቸው።

ባቀረቀርኩበት ጫማዬን እየቀጠቀጥኩ ‹ደሞ ምን ተገኘ? አልኳት የእልልታዋን ሚስጢር እንድትነግረኝ በመሻት።

‹አይ አንተ እንዳው ምን ይበጅህ ይሆን? አለችኝ።

‹ደሞ ምን አደረኩ? አልኩ ደንገጥ ብዬ..ካጎነበስኩበት ቀና እያልኩ።

‹ማናት ያቺ..እይ..ስሟ ጠፋብኝ..መርፌ ወጊ ዶፍተር ልትሆን ነው አሉ። አንተ ሰፈር ውስጥ አውደልድል። አለችኝ። እንደፈለጉ በሚሆኑብኝ አይኖቿ እየነቆረችኝ።

ተመርቄ ቤት ቁጭ በማለቴ እንደሆነ ስለገባኝ ‹ታዲያ እኔ ምን ላድርግ..ስራ አጥቼ እኮ ነው› አልኳት።

‹እዲያ መልስ እማ ታውቅበታለህ። ቤት ቁጭ ብለህ እያውደለደልክ ስራው ከየት ነው የሚገኘው? መጀመሪያ ከቤት መች ወጣህና..

‹ቆይ ማናት ዶፍተር የምትሆነው? ስል በአያቴ አማርኛ አያቴን ጠየኳት።

‹ያቺ የጎረቤታችን የጋሽ ሳህለ ልጅ ናታ..› አለችኝ።

‹ማን..ርብቃ? እንደዛሬ ጮኬ የማውቅ አይመስለኝም።

‹አዎ ናት..ምን ያስጮህሀል ታዲያ? ስትል ቆጣ አለች። ቡርቃ ናት ቡርቄ ስሟም አይያዝልኝ..ዶክተር ልትሆን ነው አሉ›አለችኝ።

‹እሷ በፍጹም ዶክተር አትሆንም። አይደለም ዶክተር ልትሆን ቀርቶ ታማ ዶክተር ፊት መቅረብ የማይገባት ሴት ናት።› አልኩ ሸንጤን ገትሬ።

‹ለምንድነው የማትሆነው? አንተ እንኳን አውደልዳዩ ማነው የምትለው ሆነህ የለ እንዴ? ድግሪ ጭነህ የለ?

‹ቆይ ዱክትርና መናገርና መስማት ለማይችሉ በነጻ መታደል ጀመረ እንዴ? ስል ድምጼን ከፍ አድርጌ ተናገርኩ።

‹ምንድነው የምትቀባዠረው! መርፌ ወጊ ልትሆን ነው ነው ያልኩህ እኮ›

‹እኔስ እሱ አይደል የገረመኝ..› አልኩ ድምጼን ሰልቤ። በአያቴ አይኖች ላይ ወደ ትላንት እየተረማመድኩ።

በርብቃ ዱክትርና ሀሳብ ዘፈቀኝ። ያኔ ጊቢ ተማሪ እያለሁ ከዶርም ጓደኞቼ ጋር አብረን ተቀምጠን ሳለ ስልኬ የርብቃን አንድ መልዕክት ተቀብሎ ነበር..‹ሀይ ማክቤል..Can I help you? ምን ማለት ነው እባክህ ትርጉሙን ንገረኝ የሚል መልዕክት። ይቺ ሴት ዶክተር ልትሆን ነው።

# ዓለም አቀፍ



## የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት የመኪና አደጋ አጋጠማቸው

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ትናንት የመኪና አደጋ እንዳጋጠማቸው ቃል አቀባያቸው ተናገሩ።ይሁንና አደጋው በፕሬዝዳንቱ ላይ ያስከተለው ይህ ነው የሚባል ጉዳት የለም።አንድ የመንገደኞች መኪና እርሳቸው ከነበሩበት መኪና፣ እንዲሁም እሳቸውን አጅቦ እየተጓዘ ከነበረ ሌላ የደኅንነት ተሽከርካሪ ጋር የተጋጨው ዘለንስኪ ኢዚዮም ከተማን ጎብኝተው ከተመለሱ በኋላ ነው።

አደጋው የደረሰውም ኪየቭ ከተማ ውስጥ እንደሆነም ተነግሯል።እርሳቸው ከነበሩበት መኪና ጋር የተላተመው ተሽከርካሪ ወዲያውኑ በአምቡላንስ ከአካባቢው እንዲርቅ ተደርጓል።ጉዳዩ አጋጣሚ ነው ወይስ የግድያ ሙከራ በሚለው ዙርያ ምንም የተባለ ነገር የለም።ሆኖም ነገሩ በጸጥታ አካላት ተይዞ ምርመራ ላይ እንደሆነ ተመላክቷል።

የ44 ዓመቱ የዩክሬን ፕሬዚሰዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ኢዝዮም የተባለችውን ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላትን ከተማ ወታደሮቻቸው ከሩሲያ ነጻ ማድረጋቸውን ተከትሎ ወደዚያው አቅንተው ነበር።በዚያ ያሉ ወታደሮቻቸውን አነቃቅተው ወደ ዋና ከተማ ኪየቭ ከደረሱ በኋላ ነው ይህ የመኪና ግጭት የተከሰተው።

ዘለንስኪ በኢዚዮም ከተማ የአገራቸው ባንዲራ ዳግም ከፍ ብሎ ሲውለበለብ በሥነ ሥርዓቱ ተገኝተው ነበር።የዩክሬን ወታደሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሩሲያ ተይዘውባቸው የነበሩ በርካታ አካባቢዎችን ነጻ እያወጡ እንደሆነ እየተዘገበ እንደሚገኝ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## የዓለም ጤና ድርጅት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሊያገረሽ እንደሚችል አስጠነቀቀ



የዓለም ጤና ድርጅት በኮቪድ-19 ስርጭት የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም ዳግም ሊያገረሽ እንደሚችል አስጠነቀቀ። ድርጅቱ ወደፊት የኮሮና ቫይረስ ሊያገረሽ እንደሚችል በመጥቀስ፥ ሀገራት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ ነቅተው በመጠበቅ ዝግጁ እንዲሆኑም አሳስቧል።

እንደ ድርጅቱ መረጃ ከፈረንጆቹ መስከረም 5 እስከ 11 ባለው ሳምንት በዓለም ዙሪያ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነፃፀር በ28 በመቶ ቀንሷል። በቫይረሱ ሳቢያ ለህልፈት የተዳረጉ ሰዎች ቁጥርም ካለፈው ሳምንት አንጻር በ22 በመቶ መቀነሱንም ነው ያመላከተው።

ድርጅቱ በመግለጫው ወረርሽኙን ለመግታት ይበልጥ መፍጠንና መጠንከር የሚገባን ጊዜ ላይ ነን ብሏል። ቫይረሱ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራጨ መሆኑን የጠቆሙት ደግሞ የዓለም ጤና ድርጅት የድንገተኛ አደጋ ፕሮግራም ቴክኒካል መሪ ማሪያ ቫን ኬርሆቭ ናቸው።

ይሁን እንጅ የስርጭቱ መጠን ለድርጅቱ ሪፖርት ከሚደረገው ቁጥር ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል። እንደ እርሳቸው ገለጻ ቫይረሱ ዓለም ላይ ሪፖርት ከሚደረገው ቁጥር በበለጠ ሁኔታ እየተዛመተ ይገኛል። ከዚህ አንጻርም ሀገራት እና ዜጎች ተገቢውን ዝግጅት እና ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል ማለታቸውን ሺንዋ መዘገቡን ያተተው ኤፍቢሲ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ዓርብ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አፄዎቹ የኮንፌዴሬሽን ዋንጫ የመልስ ጨዋታቸውን ዛሬ ያደርጋሉ

**ቦጋለ አበበ**

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ትልቁ የእግር ኳስ ውድድር መድረክ ፕሪሚየርሊግ ተሳታፊ ከመሆን አልፎ ቻምፒዮንና የዋንጫ ተፎካካሪ መሆን የቻለው ፋሲል ከነማ አገሩን ወክሎ በአፍሪካ መድረክ ተሳታፊ ሆኗል። በተለይም አፄዎቹ ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ በአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫና ቻምፒዮንስሊግ ውድድሮች አገራቸውን በመወከል በተሳትፎ ደረጃ የተሻለ ስኬት አስመዝግበዋል። በነዚህ ሦስት ዓመታት ሁለት ጊዜ የኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ላይ አንድ ጊዜ ደግሞ በቻምፒዮንስሊግ መድረክ መቅረብ ችለዋል። ካቻምና የፕሪሚየርሊጉ ቻምፒዮን በመሆን በአፍሪካ ቻምፒዮንስሊግ ኢትዮጵያን የወከሉት አፄዎቹ አምና ሁለተኛ ሆነው በማጠናቀቅ ዘንድሮ የኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ተሳታፊ መሆናቸው ይታወቃል።

በዚህ መድረክ የቅድመ ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ባለፈው ሳምንት በባህርዳር ስቴድየም ያደረጉት አፄዎቹ ካለፉት ዓመታት የተሻለ አጀማመር አሳይተዋል። አፄዎቹ ባለፈው አርብ የቡሩንዲውን ክለብ ቡማሙሩን 3ለ0 በማሸነፍ ጣፋጭ ድል ያስመዘገቡ ሲሆን፣ ዛሬ የመልሱን ጨዋታ ያከናውናሉ። አለምብርሃን ይግዛው፣ ፍቃዱ አለሙ፣ ታፈስ ሰለሞን አፄዎቹ የኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ጉዟቸውን በድል እንዲጀምሩ ግቦችን ከመረብ ያሳረፉ ተጫዋቾች ናቸው። ባለ ድሉ አሰልጣኝ ኃይሉ ነጋሽም አፄዎቹ በጨዋታው የነበራቸው የበላይነት የጠበቁትና ቡድናቸው ከዚህም የተሻለ ውጤት የማስመዝገብ አቅም እንዳለው ለሶከር ኢትዮጵያ አስተያየት ሰጥተዋል።



አፄዎቹ የዛሬውን ጨዋታ በድምር ውጤት ማሸነፍ ከቻሉ በቀጣይ የቱኒዚያውን ሴፋክሲየንን የሚገጥሙ ይሆናል፣

አፄዎቹ ዛሬ ከቡማሙሩ ጋር ላለባቸው የመልስ ጨዋታ በአዲስ አበባ ሲዘጋጁ የቆዩ ሲሆን፣ ከቀናት በፊት ጨዋታው ወደ ሚካሄድበት ገለልተኛ አገር ታንዛኒያ አቅንተዋል፡፡ ቡሩንዲ የመልሱን ጨዋታ ለማስተናገድ በካፍ ፍቃድ የተሰጠው ስቴድየም የሌላት በመሆኑ ቡማሙሩ ክለብ አፄዎቹን በገለልተኛ ሜዳ ለመግጠም ተገደዋል። የመልሱ ጨዋታ የሚካሄደው ደግሞ በታንዛኒያ አዛም ኮምፕሌክስ ሜዳ ላይ ነው፡፡ ጨዋታው በገለልተኛ ሜዳ መካሄዱ አፄዎቹ በሜዳቸው በሰፊ ግብ ልዩነት ከማሸነፋቸው ጋር ተደምሮ ወደ ቀጣዩ ዙር ለማለፍ ጥሩ ዕድል እንደሚፈጥርላቸው ይጠበቃል፡፡ አፄዎቹ ይህንን ጨዋታ በድምር ውጤት የሚያሸንፉ ከሆነ በቀጣይ የቱኒዚያውን ሴፋክሲየንን እንደሚገጥሙ አስቀድሞ የወጣው መርሐ ግብር ይጠቁማል።

የፋሲል ከነማ ስፖርት ክለብ ዋና አሰልጣኝ ኃይሉ ነጋሽ ከክለቡ ማህበራዊ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ «ባህርዳር ላይ ጨዋታችንን ከማድረጋችን በፊት ከተጫዋቾቼ ጋር ተነጋግረናል። የተነጋገርነውም በተቻለ መጠን በሜዳችንና በደጋፊያችን ፊት ውጤቱን ጨርሰን ለመውጣት የምችለውን ለማድረግ ነበር። በተነጋገርነው መሠረትም እቅዳችንን አሳክተናል። ዛሬ የምናደርገውን ጨዋታም ቢቻል አሸንፈን አለበለዚያም ውጤታችንን አስጠብቀን የምንወጣበትን መንገድ ነው የምናስበው፣ ነገር ግን ዋነኛው አላማችን ቡድናችን ጨዋታውን አሸንፎ ወደሚቀጥለው ዙር እንዲያልፍ ማስቻል ነው። ያንን ለማድረግ ሁላችንም ዝግጁ ነን» ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከመጀመሪያው ጨዋታ ውጤት አንፃር የዛሬው ጨዋታ ያለቀ ሊመስል ይችላል ያሉት አሰልጣኙ፣ የእግርኳስ ውጤቶች በባህሪያቸው አይታወቁምና ቡድናቸው በጥንቃቄ እንደሚጫወት ገልፀዋል፡፡ በቡድናቸው ቅርፅ ዙሪያ ግን ጨዋታው እስከሚደረግበት ሰዓት ድረስ የተጫዋቾችን ደህንነት ተመልከተው መጨረሻ ላይ እንደሚወስኑ አስረድተዋል፡፡

የቡድኑና አጠቃላይ የተጫዋቾቹ መንፈስ እንዲሁም መነቃቃት ጥሩ ነው ብለው እንደሚያስቡ የገለፁት አሰልጣኙ፣ የመጀመሪያውን ጨዋታ ከማድረጋቸው በፊትም የተጫዋቾቹ የመጫወት ፍላጎትና ውጤት ለማምጣት ያላቸው ተነሳሽነት በጣም ጥሩ እንደነበር አስታውሰዋል። በዛሬው ጨዋታም ያንን መንፈስ ለማስቀጠል በጋራ እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

«በ2015 የውድድር ዘመን ካቀድናቸው ዋነኛ እቅዶች መካከል አንዱ አሁን በምንወዳደርበት የአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ረዥም የሚባል ጉዞን ማድረግ ነው። በዚህ መነሻም የመጀመሪያውን ዘጠና ደቂቃ በጥሩ ውጤት ጨርሰናል። በቀጣይም የሚኖሩን ጨዋታዎችን በድል በመወጣት በክለቡ የታሪክ መዝገብ ላይ አዲስ ነገር ለማስፈር እናስባለን። ነገር ግን ቅድሚያ የምንሰጠው በእጃችን ላይ ያሉ ጨዋታዎችን በድል ለመቋጨት በትኩረት መንቀሳቀስ ላይ ነው። ይሄንን ለማድረግ ደግሞ በተጫዋቾችም ሆነ በአሰልጣኞች ውስጥ ጥሩ መነቃቃት አለ» በማለት አሰልጣኙ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን በካፍ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ላይ ቢወክሉም የመጀመሪያዎቹን ቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች ግን ማለፍ እንዳልቻሉ ይታወሳል፡፡ ዘንድሮ ግን ይህን ታሪክ ለመቀየር ጥሩ አጀማመርና ተነሳሽነት አሳይተዋል፡፡

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቀያ

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ማረሚያ ቤቶች አስ/ር ኮሚሽን በጎፋ ዞን የሣውላ ማረሚያ ተቋም በ2015 በጀት ዓመት ከዚህ በታች በሎት የተከፋፈሉትን ግዥዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1. የጽህፈት መሣሪያና የጽዳት ዕቃዎች
ሎት 2. ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች
ሎት 3. የህንፃ መሣሪያዎች

ስለሆነም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. በዘርፉ የንግድ ፈቃድ ያለው
2. የዘመኑን ግብር የከፈለ
3. የግብር ከፋይ መለያ /TIN/ ቁጥር ያለው
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ የቫት ተመዝጋቢ የሆነ
5. በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የምዝገባ የምስክር ወርቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማረሚያ ተቋም ስም በCPO ወይም በጥሬ ገንዘብ ለሎት-1 7,500.00፣ ለሎት-2 6,000.00፣ ለሎት-3 7,500.00 ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች ከ1 እስከ 5 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች እና የማጫረቻ ሠነድ ኦሪጅናልና ኮፒ በተለያዩ ፖስታ ውስጥ አስገብቶ በአንድ እናት ፖስታ ውስጥ በታሸገ ኤንቨሎፕ ለዚህ በተጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በመንግስት የሥራ ሰዓት ማስባት አለባቸው፡፡
8. የጨረታ ማስታወቂያ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ለ15 ቀናት በአየር ላይ የሚቆይ ሲሆን የጨረታ ሣጥኑ በ15ኛው ቀን ከሰዓት 11:30 ላይ ታሽጎ በ16ኛው ቀን 2:30 ላይ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፤ ዕለቱ ቅዳሜ፣ እሁድ ወይም በዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው ቀን በመንግስት የሥራ ሰዓት ይከፈታል፡፡
9. የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የሣውላ ማረሚያ ተቋም የግዥ ፋ/ን/አስ/ር ደጋፊ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 9 በመቅረብ የማይመለስ 100/አንድ መቶ/ ብር በመክፈል የጨረታ ሠነድ መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
10. ተጫራቾች ዕቃውን በራሳቸው ወጪ እስከ ሣውላ ማረሚያ ተቋም አምጥተው ማስረከብ አለባቸው፡፡
11. ተጫራቾች የጽህፈት መሣሪያ ጥራት ማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የእስክሪብቶ እና የወረቀት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡
12. የጨረታው አሸናፊ ሆነው የተገኙ ተጫራቾች የዕቃዎችን አጠቃላይ ዋጋ በ10 % ቼክ ወይም /CPO/ የውል ማስከበርያ በማስያዝ ከሳውላ ማረሚያ ተቋም ግዥ ፋ/ን/አስ/ር ደ/ሥራ ሂደት ጋር የውል ስምምነት መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡
13. በሌሎች ተጫራቾች ዋጋ ላይ ተንተርሶ መወዳደር ተቀባይነት የለውም፡፡
14. ማረሚያ ተቋሙ የተሻለ አማራጭ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ መሉ በመሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ማረሚያ ቤቶች አስ/ር ኮሚሽን**
**የሣውሳ ማረሚያ ተቋም**

ETHIOPIAN SHIPPING & LOGISTICS

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ መስያ ቁጥር፡- ESLSE/MM/NCB/07/2015

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ወደቦች እና ቦንድድ መጋዘኖች ከሦስት ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት ግዥን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማግኘት ይፈልጋል፡፡
በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ በዘርፉ የተሰማራችሁ የጭነት ትራንስፖርት ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት እንደትሳተፉ እንጋብዛለን፡፡

1. በዘርፉ የተሰማሩ ሁሉም ድርጅቶች ከትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር/ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የታደሰ የጭነት አገልግሎት የደረጃ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የታደሰ የተሸከርካሪዎች ዝርዝር መረጃ፤
2. የንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት እና የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፊኬት፤
3. የንግድ ትራንስፖርት ድርጅቶች ጊዜው ያላለፈበት ጨረታን ለመሳተፍ የሚያስችል የግብር አከፋፈል የምስክር ወረቀት ማስረጃ /Tax Clearance Certificate/
4. ተጫራች ድርጅቶች የንግድ፣ የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ሰነዶችን በተለያየ ፖስታ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራች ድርጅቶች የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/በCPO ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና 'ETHIOPIAN SHIPPING & LOGISTICS SERVICES ENTERPRISE' በሚል ስም በማሰራት ከቴክኒካል ፖስታው ጋር ወይም ለብቻው ጨረታው ሳይከፈት በማቅረብ መጫረት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራች ድርጅቶች የጨረታ ሰነዱን ለመግዛት ለገሃር በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት 3ኛ ፎቅ የፋይናንስ ክፍል የማይመለስ ብር 150/አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን 10ኛ ፎቅ በግዥ መምሪያ ከሀገር ውስጥ ግዥ ዋና ክፍል መውሰድ ይችላሉ፡፡
7. ጨረታው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለገሃር በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት ሁሉገብ ሕንፃ 10ኛ ፎቅ ግዥ መምሪያ አዳራሽ መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡፡00 ተዘግቶ በዚሁ እለት 8፡30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
8. ከጨረታ መከፈቻው ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
9. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር** 0115549786/0115549781

**የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ